# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ፍትሕ ቢሮ እና ተጠሪ ተቋማት

# የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

ነሀሴ 2015 ዓ/ም

## ማውጫ

**ርዕስ** **ገጽ**

ክፍል አንድ ... 4
1. የሶስት ዓመት (ከ2013 እስከ 2015 ዓ/ም) የመሪ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ... 4
1.1. የመደበኛ፣ የሙስና እና የታክስና ኢኮኖሚ የወንጀል ... 4
1.2. በሴቶች፣ ሕጻናት፣ አረጋውያንና በአካል ጉደተኞች የተፈጸሙ የወንጀል መዝገቦች ... 5
1.3. የተመዘበረ ሀብት ማስመለስን በተመለከተ ... 6
1.4. የህግ ጥናት ማርቀቅና ማስረጽ ሥራ ... 7
1.5. የጠበቆች ሲቪል ማህበራትና ሰነዶች ምዝገባ ስራ ... 7
1.6. የህግ ታራሚዎች ማረምና ማነጽ ሥራ ... 7
1.7. የህግ ባለሙያዎች ስልጠናና የህግ ምርምራ ስራ ... 8
ክፍል ሁለት ... 17
ተቋማዊ ዳሰሳ ... 17
2.1 የተቋማቱ ተግባርና ኃላፊነት *(በነባሩ ክልል)* ... 17
2.1.1 የፍትህ ቢሮ ስልጣንና ተግባር ... 17
2.1.2 የማረሚያ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት ... 20
2.1.3 የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠናና የህግ ምርመር ማዕከል ተግባርና ኃላፊነት ... 21
2.2 የተቋማቱ ማስፈፀሚያ ተቋማዊ አቅም፣ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ... 21
2.2.1 የሕገ መንግስት፣ ሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነዶች ቅኝት፣ ... 21
2.3 የተቋማቱ ተገልጋይ እና ባለድርሻ አካላት ትንተና ... 25
2.4 የተቋማዊ ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚና ስጋቶች *(በነባሩ ክልል በነበሩበት ወቅት)* ... 32
ክፍል ሶስት ... 45
የሰባት ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ (ከ2016 እስከ 2022 ዓ/ም) ... 45
3.1. የዕቅዱ መነሻ፣ ዓላማ፣ አስፈላጊነት እና ወሰን ... 45
3.2. የትኩረት አቅጣጫዎች ... 46
3.3. ማስፈፀሚያ ስልቶች ... 46
3.4. የ7 ዓመታት ስትራቴጂክ ዕቅድ ዋና ዋና ግቦችና ተኮር ተግባራት ... 46
3.5. የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ግቦች፣ የግብ አመልካቶችና ዒላማዎች ... 54
ክፍል አራት ... 60
4. የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስርዓት ... 60
4.1. የክትትልና ግምገማው ዓላማ፡- ... 60
4.2. የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ስርዓት ... 60

## መግቢያ

የነባሩ ክልል (የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል) ፍትሕ ቢሮ፣ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮምሽን እና የሕግ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ተቋም በሕግ የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት ተግባራዊ በማድረግ የክልሉ ሕዝብና መንግሥት የጣለባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ስትራቴጂያዊ ዕቅድ አፈጻጸም መነሻነት የተቋማቱ የ10 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ በማዘጋጀት በማዘጋጀት ከ2013 በጀት ዓመት እስከ 2015 በጀት ዓመት ድረስ ሲተገበር ቆይቷል፡፡

ነገር ግን በደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ስር ይገኙ የነበሩ መዋቅሮች በህዝበ ውሳኔ በሶስት ክልሎች ማለትም ሲዳማ ክልል፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል መመስረታቸውን ተከትሎ ነባሩ ክልል እራሱን በአዲስ መልክ በ7 ዞኖች እና በ3 ልዩ ወረዳዎች በመደራጀት ነሀሴ 13/2015 ዓ.ም "የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል" በሚል በመመስረቱ የተቋማቱ (የፍትህ ሴክተር) የ7 ዓመት (ከ2016 እስከ 2022 ዓ/ም የሚተገበር መሪ የልማት ዕቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም የክልሉ ፍትህ ቢሮ፣ ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን እና የሕግ ባለሙያዎች ማሰልጠኛና የሕግ ምርምር ተቋም የማዕ/ኢት/ክልል ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ ባደረገ መልኩ የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ እንደሚከተለው ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## 1. የሶስት ዓመት (ከ2013 እስከ 2015 ዓ/ም) የመሪ የልማት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ

### 1.1. የመደበኛ፣ የሙስና እና የታክስና ኢኮኖሚ የወንጀል

**የወንጀል ምርመራ መዝገቦች በተመለከተ፡-** ባለፉት ሶስት ዓመታት ከፖሊስ ምርመራ ተጣርቶ ለዐቃቤ ህግ የቀረቡ 46,479 የምርመራ መዝገቦች መካከል በ45,887 ላይ በዐቃቤ ህግ የተለያየ ውሳኔ የሰጠባቸው ሲሆን ውሳኔውም ክስ የተመሰረተባቸው 38,252፣ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/42/1/ሀ መሰረት የተዘጋ 1,016፣ በዐቃቤ ሕግ በዕርቅ ያለቁ 5,227፣ በወ/መ/ሥ/ሥ//ህ/ቁ/38/ሐ መሰረት ለተጨማሪ ምርመራ ለፖሊስ የተመለሰ 1,016፣ ስልጣን ላለው አካል የተላከ 376 መዝገቦች ናቸው፡፡ ቀሪ 592 መዝገቦች ወደ 2016 ተሻግረዋል፡፡ በመሆኑም የ3 ዓመት አማካይ የማጥራት ምጣኔ 97.7% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸም 94.7% ሲሆን አፈጻጸሙ ከዕቅድ ጋር ሲነጻጸር 96.9% ተሳክቷል፡፡

**በመደበኛ ፍ/ቤት የመዝገቦች ክርክር በተመለከተ፡-** ባለፉት ሶስት የዕቅድ ዘመናት በፍ/ቤት ክስ በመመስረት ክርክር የተደረገባቸው ከ2012 ወደ 2013 በጀት ዓመት የዞረ 2,255 በዕቅድ ዘመኑ አዲስ ክስ የቀረበ 38,252 በድምሩ 40,507 መዝገቦች ሲሆኑ ከነዚህ መካከል በ39,610 ላይ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ውሳኔውም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተላለፈባቸው 29,117፣ በፍ/ቤት በዕርቅ የተጠናቀቁ 7,065፣ ተከሳሽ በነጻ የተሰናበተበት 1,335፣ ምስክርና ተከሳሽ ባለመቅረባቸው የተዘጋ 2,083 እና ለሕዝብና ለመንግስት ጥቅም ሲባል የተቋረጠ 10 መዝገቦች ናቸው፡፡ ቀሪ 897 መዝገቦች በፍ/ቤት በቀጠሮ ወደ 2016 በጀት ዓመት ተሻግረዋል፡፡ በመሆኑም የመርታት ምጣኔ በአማካይ 95.3% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 91.4% ሲሆን አፈጻጸሙ ከዕቅድ ጋር ሲነጻጸር 96% ተሳክቷል፡፡ የምስክርና ማስረጃ በማጣት ሚቋረጡ መዝገቦች ምጣኔ ወደ 3.6% ለመቀነስ ታቅዶ አፈጻጸሙ ወደ 5.1% ዝቅ ያለ ሲሆን ይህም የዕቅድ 70.3% ተሳክቷል፡፡

ዕርቅ በተመለከተ፡- ቢሮው በርእርቅ ማለቅ የሚገባቸው ቀላል ወንጀሎች 65%ቱ ክስ ሳይመሰረት በእርቅ ለመጨረስ አቅዶ በዕቅድ ዘመኑ በዐቃቤ ህግ በዕርቅ ያለቁ 5,027 ጉዳዮች ሲሆኑ በፍ/ቤት ደግሞ 7,065 ጉዳዮች በድምሩ 12,092 ጉዳዮች በዕርቅ ተጠናቀዋል፡፡ በመሆኑም አፈጻጸሙ 41.1% ሲሆን አፈጻጸሙ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር 63.2% ሆኗል፡፡

**የይግባኝ መዝገቦች በተመለከተ፡-** በ3 ዓመት 4,008 ይግባኝ የተጠየቀ ሲሆኑ 1,027 በዐቃቤ ሕግ እና 2,981 ደግሞ በተከሳሽ የተጠየቁ ናቸው፡፡

- **በዐቃቤ ሕግ** ከተጠየቁ ይግባኝ መካከል በ954 ላይ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ውሳኔውም ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባለበት 354፣ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የፀና 217፣ ተሻሽሎ የተወሰነ 378 እና 5 መዝገቦች የተቋረጡ ናቸው፡፡ ቀሪ 73 በፍ/ቤት በቀጠሮ ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ጥፋተኛ የማሰኘት ምጣኔ በአማካይ 87% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸም 76.6% ሲሆን አፈጻጸሙ ከዕቅድ አንጻር 88% ማድረስ ተችሏል፡፡
- **በተከሳሽ ከተጠየቁ** ይግባኝ መካከል በ2,796 ላይ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ውሳኔውም ተከሳሽ በነጻ የተሰናበተበት 227፣ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የፀና 1,492፣ ተሻሽሎ የተወሰነ 1,025 እና 2 መዝገብ ደግሞ ተቋርጧል፡፡ ቀሪ 185 በቀጠሮ ላይ ይገኛሉ፡፡ ተከሳሽ ይግባኝ የጠየቀባቸው የማፀናት ምጣኔ በአማካይ 96.25% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸም 90% ሲሆን ከዕቅድ አንጻር 93.5% ተሳክቷል፡፡

**የሰበር መዝገቦች በተመለከተ፡-** በሶስት ዓመት ውስጥ 646 ሰበር የተጠየቀ ሲሆን እነዚህም 177 በዐቃቤ ሕግ እና 503 ደግሞ በተከሳሽ የተጠየቁ ናቸው፡፡

- **በዐቃቤ ሕግ ከተጠየቁ** ሰበር መካከል በ144 መዝገቦች ላይ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ውሳኔውም ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባለበት 40፣ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የፀና 44 እና ተሻሽሎ የተወሰነ 60 መዝገቦች ናቸው፡፡ ቀሪ 33 መዝገቦች ወደ 2016 በጀት ዓመት በፍ/ቤት በቀጠሮ ተሻግረዋል፡፡ በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ ሰበር የጠየቀባቸው መዝገቦች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የማሻር ምጣኔ በአማካይ 82% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸም 69.5% ሲሆን አፈጻጸሙ ከዕቅድ ጋር ሲነጻጸር 84.8% ተሳክቷል፡፡
- **በተከሳሽ ከተጠየቁ** ሰበር መካከል በ428 ላይ ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ውሳኔውም ተከሳሽ በነጻ የተሰናበተበት 53፣ የፀና 216 እና ተሻሽሎ የተወሰነ 159 መዝገቦች ናቸው፡፡ ቀሪ 75 መዝገቦች ወደ 2016 በቀጠሮ ተሻግረዋል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የማፀናት ምጣኔ በአማካይ 93.5% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸም 87.5% ሲሆን ይህም ከዕቅድ ጋር ሲነጻጸር 93.6% ማድረስ ተችሏል፡፡

### 1.2. በሴቶች፣ ሕጻናት፣ አረጋውያንና በአካል ጉደተኞች የተፈጸሙ የወንጀል መዝገቦች

**የወንጀል ምርመራ መዝገቦች በተመለከተ፡-** ባለፉት ሶስት ዓመታት በፖሊስ የወንጀል ምርመራ ተጣርቶ 4,901 መዝገቦች ለዐቃቤ ህግ ቀርበው በ4,830 የምርመራ መዝገቦች ላይ ዐቃቤ ህግ የተለያየ ውሳኔ የሰጠባቸው ሲሆን ውሳኔውም ክስ የተመሰረተባቸው 3,813፣ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/42/1/ሀ መሰረት የተዘጋ 148፣ በዐቃቤ ሕግ በዕርቅ ያለቁ 310፣ በወ/መ/ሥ/ሥ//ህ/ቁ/38/ሐ መሰረት ለተጨማሪ ምርመራ ለፖሊስ የተመለሰ 559 ናቸው፡፡ ቀሪ 71 መዝገቦች ወደ 2016 ተሻግረዋል፡፡ በመሆኑም የ3 ዓመት አማካይ የማጥራት ምጣኔ 100% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸም 87.2% ደርሷል፡፡

**በመደበኛ ፍ/ቤት የመዝገቦች ክርክር በተመለከተ፡-** ባለፉት ሶስት የዕቅድ ዘመናት በፍ/ቤት ክስ በመመስረት ክርክር የተደረገባቸው 3,813 መዝገቦች ሲሆኑ ከነዚህ መካከል በ3,284 ላይ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ውሳኔውም የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የተላለፈባቸው 3,113 እና ተከሳሽ በነጻ የተሰናበተ 69 መዝገቦች ናቸው፡፡ ቀሪ 529 መዝገቦች ቀጠሮ ወደ 2016 በጀት ዓመት ተሻግረዋል፡፡ በመሆኑም የመርታት ምጣኔ በአማካይ 96% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸም 94.9% ሲሆን አፈጻጸሙ ከዕቅድ አንጻር 98.8% ተሳክቷል፡፡ የሚንጠባጠቡ መዝገቦች ምጣኔ ወደ 2.8% ለመቀነስ ታቅዶ አፈጻጸሙ ወደ 2.9% ዝቅ ያለ ሲሆን ይህም የዕቅድ 106% ተሳክቷል፡

**የይግባኝ መዝገቦች በተመለከተ፡-** በ3 ዓመት 39 ይግባኝ የተጠየቀ ሲሆኑ 19 በዐቃቤ ሕግ እና 20 ደግሞ በተከሳሽ የተጠየቁ ናቸው፡፡ **በዐቃቤ ሕግ** ከተጠየቁ ይግባኝ መካከል በ18 ላይ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ውሳኔውም ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባለበት 9፣ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የፀና 1፣ ተሻሽሎ የተወሰነ 8 ይግባኞች ናቸው፡፡ ቀሪ 1 በፍ/ቤት በቀጠሮ ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ጥፋተኛ የማሰኘት ምጣኔ በአማካይ 96.3% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸም 95.2% ሲሆን አፈጻጸሙ ከዕቅድ አንጻር 98.9% ማድረስ ተችሏል፡፡ **በተከሳሽ ከተጠየቁ** ይግባኝ መካከል በ15 ላይ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡ ውሳኔውም ተከሳሽ በነጻ የተሰናበተበት 2፣ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የፀና 11፣ ተሻሽሎ የተወሰነ 2 መዝገቦች ናቸው፡፡ ቀሪ 5 በቀጠሮ ላይ ይገኛሉ፡፡ ተከሳሽ ይግባኝ የጠየቀባቸው የማፀናት ምጣኔ በአማካይ 97.3% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸም 86.7% ሲሆን ከዕቅድ አንጻር 89% ተሳክቷል፡፡

**የሰበር መዝገቦች በተመለከተ፡-** በሶስት ዓመት ውስጥ 5 መዝገቦች ላይ ሰበር የተጠየቀ ሲሆን እነዚህም 2 በዐቃቤ ሕግ እና 3 ደግሞ በተከሳሽ የተጠየቁ ናቸው፡፡

**በዐቃቤ ሕግ የተጠየቁ** 2 መዝገቦች ላይ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን ውሳኔውም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ፀንቷል፡፡ በመሆኑም ዐቃቤ ሕግ ሰበር የጠየቀባቸው መዝገቦች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የማሻር ምጣኔ በአማካይ 96.3% ለማድረስ የታቀደ ቢሆንም የተጠየቁ ሰበሮች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ በጽናቱ ዕቅዱ አልተሳካም፡፡ **በተከሳሽ ከተጠየቁ** ሰበር መካከል በ2 ላይ ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ውሳኔውም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የፀና ሲሆን 1 መዝገብ ወደ 2016 በቀጠሮ ተሻግረዋል፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የማፀናት ምጣኔ በአማካይ 97.3% ለማድረስ ታቅዶ አፈጻጸም 100% ማሳካት ተችሏል፡፡

### 1.3. የተመዘበረ ሀብት ማስመለስን በተመለከተ

- **በሙስና የተመዘበረ ሀብት በተመለከተ**

በሶስቱ የዕቅድ ዘመናት በሙስና ምዝበራ ተፈጽሞ የቀረበ ገንዘብ 403,954,022.79 ብር ሲሆን ክስ በመመስረትና ክርክር በማድረግ 321,095,499.49 ብር ለመንግስት ማስመለስ ተችሏል፡፡ ቀሪ 82,858,671.29 ብር በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም 82% ለማስመለስ ታቅዶ አፈጻጸሙም 79% ሲሆን የዕቅዱ 96% ማሳካት ተችሏል፡፡

- **በታክስ የተመዘበረ ሀብት በተመለከተ፡-**

በሶስቱ የዕቅድ ዘመናት በታክስ ማጭበርበርና ስወራ ተፈጽሞ የቀረበ ገንዘብ 22,263,389.79 ብር ሲሆን በክስና በድርድር 13,997,972.07 ብር ለመንግስት ማስመለስ ተችሏል፡፡ ቀሪ 8,265,417.72 በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም 96% ለማስመለስ ታቅዶ አፈጻጸሙም 64.5% ሲሆን የዕቅዱ 67.5% ማሳካት ተችሏል፡፡

- **በውል አስተዳደር የባከነ ሀብት/ፍትሐብሔራዊ ጉዳይ/ በተመለከተ፡-**

**መንግስት በከሰሰባቸው ፍትሐብሔር ጉዳዮች በተመለከተ፡-** በተለያዩ ተቋማትና የልማት ድርጅቶች በውል አስተዳደር የባከነ ገንዘብ በሶስት ዓመት ውስጥ 3,786 መዝገቦች የያዙት ገንዘብ መጠን 1,866,273,389.98 ብር ቀርቦ በ3,688 መዝገብ የያዙት የገንዘብ መጠን 1,251,955,262.93 ብር ላይ ክስ በመመስረትና በመከራከር በፍ/ቤት ውሳኔ ብር 1,192,083,301.93 እና በድርድር 200,621,064.58 ብር በድምሩ 1,392,704,366.50 ብር ለመንግስት ገቢ የተደረገ ሲሆን ቀሪው በፍ/ቤት በሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም 91% ለማስመለስ ታቅዶ አፈጻጸሙም 74.7% ማስመለስ ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙ ከዕቅድ ጋር ሲነጻጸር 82.5% ማሳካት ተችሏል፡፡ ከባከነ ሀብት ላይ በአማካይ 11% በድርድር ለማስመለስ ታቅዶ አፈጻጸሙ 13.4% ማሳካት ተችሏል፡፡

**መንግስት በተሰሰባቸው ፍትሐብሔር ጉዳዮች በተመለከተ፡-** በሶስት ዓመት ውስጥ መንግስት የተከሰሰበት 476 መዝገቦች የያዙት የገንዘብ መጠን 444,515,241.39 ብር ላይ ፍ/ቤት ቀርቦ በመከራከር በ373 መዛግብት የያዙት የገንዘብ መጠን ብር 264,860,389.20 ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን ውሳኔውም 351 መዝገብ የያዙት ገንዘብ 243,552,022.05 ብር መንግስት እንዳይከፍል ማስወሰን የተቻለ ሲሆን በ22 መዝገብ የያዙት ገንዘብ 21,311,067.15 ብር ለተከሳሽ ተወስኗል፡፡ በመሆኑም 91.5% መንግስት አላግባብ ሊከፍ ሀብት የነበረ ሀብት ማዳን ተችሏል፡፡

**በዐቃቤ ህግ እና በፍ/ቤት ውሳኔ** ከተሰጠባቸው መዝገቦች መካከል በናሙናነት በተመረጡ 967 የወንጀልና የፍትሐብሔር መዝገቦችን የህግ ኦዲት በማድረግ የአፈጻጸም ጥራታቸው ለማረጋገጥ ታቅዶ 1,039 መዝገቦች ላይ የህግ ኦዲት ሥራ የተሰራ ሲሆን አፈጻጸሙም 107% ማሳካት ተችሏል፡፡

### 1.4. የህግ ጥናት ማርቀቅና ማስረጽ ሥራ

**የንቃተ ህግ ግንዛቤ ትምህርትን በተመለከተ፡-** በየበጀት ዓመቱ 1 ጊዜ የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ በዓመት በአማካይ 65 ማንዋል ለማዘጋጀት ታቅዶ 38 ማስተማሪያ ማንዋሎች የተዘጋጁ ሲሆን በእነዚህ ማንዋሎች የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ለ2,890,417 የህብረተሰብ ክፍሎች የንቃተ ህግ ትምህርት ለመስጠት ታቅዶ ለ2,869,884 የህብረተሰብ ክፍሎች ግንዘቤ ተፈጥሯል፡፡ አፈጻጸሙም 95.5% ማሳካት ተችሏል፡፡

**የህግ ማርቀቅና ቅርጽ ማስያዝን በተመለከተ፡-** ባለፉት ሶስት ዓመት እንዲረቀቁና አስተያየት እንዲሰጥባቸው የቀረቡ 12 አዋጆች፣ 28 ደንቦች እና 33 መመሪያዎች በሙሉ የማርቀቅና የህግ ቅርጽ የማስያዝ ስራ ተሰርቷል፡፡ አፈጻጸሙ 100% ማሳካት ተችሏል፡፡

### 1.5. የጠበቆች ሲቪል ማህበራትና ሰነዶች ምዝገባ ስራ

**የጥብቅና ፈቃድ ዕድሳትና አዲስ ፈቃድ መስጠት አገልግሎት በተመለከተ፡-** ከተቋሙ የጥብቅና ፍቃድ ከማደስ አንጻር በየበጀት ዓመቱ በአማካይ 339 ጠበቆች ፈቃዳቸውን ለማደስ ታቅዶ በአማካካ 304 ጠበቆች ፈቃዳቸው አሳድሰዋል፡፡ አፈጻጸሙም 89.7% ነው፡፡ እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመት በተቋሙ የሚዘጋጀውን የብቃት ምዘና ፈተና ወስደው ያለፉትን ለ120 የሕግ ባለሙያዎች አዲስ የጥብቅና ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል ዜጎች ለጠበቃ ለመክፈል አቅም በማጣት ፍትህ የማግኘት መብታቸው እንዳይጓደል በግል ጠበቆች፣ በክልሉ በሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች 3 የህግ ፋካሊቲዎች አማካኝነት ባለፉት ሶስት ዓመት 9,127 የህብረተሰብ ክፍሎች ነጻ የጥብቅና እና የህግ ድጋፍ አገልግሎት አግኝተዋል፡፡

**የሲቪል ማህበራት ፈቃድ ዕድሳትና አዲስ መስጠት አገልግግት በተመለከተ፡-** ከተቋሙ ሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የወሰዱ ማህበራት ፈቃድ ከማደስ አንጻር በየበጀት ዓመቱ በአማካይ 52 ማህበራት ፈቃዳቸውን ለማደስ ታቅዶ ሙሉ ለሙሉ ማደስ ተችሏል፡፡ እንዲሁም ባለፉት ሶስት ዓመት አዲስ የሰውነት ማረጋገጫ ፈቃድ ይሰጠኝ ጥያቄ ያቀረቡ 35 ማህበራት ፈቃድ ተሰጥቷል፡፡

በዕቅድ ዘመኑ ሕግን ተከትለው የቀረቡ 33,257 ሰነዶችን ሙሉ ለሙሉ የማረጋገጥ ስራ ተሰርቷል፡፡ በመሆኑም በጠበቆችና በሲቪል ማህበራት ፈቃድ ዕድሳት እና ከሰነድ ማረጋገጥ አገልግሎት በአጠቃላይ 11,196,006 ብር ለመንግስት ገቢ ማድረግ ተችሏል፡፡

### 1.6. የህግ ታራሚዎች ማረምና ማነጽ ሥራ

**በክልሉ** ከሚገኙ 7 ማረሚያ ተቋማት ባለፉት ሶስት ዓመት በተደረገው የይቅርታ አሰጣጥ 4,051 የህግ ታራሚዎች ይቅርታ ተፈተው ወደ ሕብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ተደርጓል፡፡ በየበጀት ዓመቱ በአማካይ 2,135 የህግ ታራሚዎች በመደበኛ ትምህርት ፕሮግግም ለማስተማር ታቅዶ 2,149 ታራሚዎች የቀለም ትምህርት እንዲማሩ እየተደረገ ይገኛል፤ አፈጻጸሙም 100% ማሳካት ተችሏል፡፡ እንዲሁም 1,756 ታራሚዎች በተለያዩ የዕደ ጥበባት ሙያዎች እንዲሰለጥኑ ለማድረግ ታቅዶ 1,849 ታራሚዎች ማሰልጠን ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ለ2,987 ታራሚዎች የምክር አገልግሎት ለመስጠት ታቅዶ 2,816 ታራሚዎች የምክር አገልግሎት ያገኙ ሲሆን አፈጻጸሙም 94.3% ተሳክቷል፡፡ በተጨማሪም 3,113 ታራሚዎች የሥነ ዜጋና ሥነ-

ምግባር ትምህርት ለማሰልጠን ታቅዶ 3,207 ስልጠናውን አግኝተዋል፡፡ ለ60 ታራሚዎች ደግሞ የኮ-ካውስለርነት ስልጠናውን ለመስጠት ታቅዶ 52 ታራሚዎች ማሰልጠን ተችሏል፡፡ አፈጻጸሙም 87.2% ደርሷል፡፡ እንዲሁም ለ8,207 ታራሚዎች በወንጀል አስከፊነት ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዶ ለ8,273 ታራሚዎች ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡

የታራሚዎች ደህንነትና ሰብዓዊ መብት አያያዝ ከማሻሻል አንጻር በሶስት ዓመት ውስጥ 135 የፖሊስ አባሎች የተሀድሶ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ96 አባላት ስልጠና የተሰጠ ሲሆን አፈጻጸሙ 71% ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም 373 አዲስ ምልምል የፖሊስ አባላት ለማሰልጠን ታቅዶ 235 አባሎች እንዲሰለጥኑ ተደርጓል፤ አፈጻጸሙም 63% ነው፡፡

### 1.7. የህግ ባለሙያዎች ስልጠናና የህግ ምርምራ ስራ

**በፍትህ አካላት የስልጠናና የህግ ምርምር ማዕከል** በሶስት ዓመት ውስጥ የቅድመ ሥራ ሠልጣኞች መስፈርቱን ያሟሉ 195 የህግ ባለሙያዎች ለማሰልጠን ታቅዶ 180 ባለሙያዎች ማሰልጠን ተችሏል፤ አፈጻጸሙም 92.3% ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም 175 በስራ ላይ የሚገኙ ዳኞችና ዐቃብያነ ህግ የስራ ላይ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ 136 በማሰልጠን ወደ ስራ ተመልሰዋ፤ አፈጻጸሙም 78%፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ የህግ ርዕሰ ጉዳዮች ለ429 የህግ ባለሙያዎች አጫጭር ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ለ350 ባለሙያዎች መስጠት ተችሏል አፈጻጸሙ 81.7% ደርሷል፡፡

በሌላ በኩል በየበጀት ዓመቱ 1 ጊዜ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ በጥናት በተለዩ 7 የሕግ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥናትና ምርምር ለማድረግ ታቅዶ በ4 ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥናት በማድረግ ለሚመለከተው አካል ለግብዓት እንዲሆን መስጠት ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በፍትህ ተቋማት የሚከናወኑ የፍትህ ማሻሻያ ስራዎች አፈጻጸም ላይ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የማማከርና የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፡፡

# የ3 ዓመት (2013 እስከ 2015 ዓ/ም) የዋና ዋና የፍትህ ስራዎች ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

| የአፈጻጸም አመልካቾች | መነሻ ዓመት 2012 | | የ2013 ዕቅድ | | የ2013 አፈፃፀም | | የ2014 ዕቅድ | | የ2014 አፈፃፀም | | የ2015 ዕቅድ | | የ2015 አፈፃፀም | | የሦስት ዓመት አማካኝ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2013 አፈጻጸም | 2013 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2014 አፈጻጸም | 2014 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2015 አፈጻጸም | 2015 አፈጻጸም በመቶኛ | የሦስት ዓመት አማካኝ ዕቅድ | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም በመቶኛ |
| ከፖሊስ ጋር በጋራ የተጣራ የወንጀል ምርመራ ምጣኔ፣ | 95.80% | 95.80% | 100% | 100% | 94% | 94% | 100% | 100% | 90% | 90.0% | 100% | 100% | 95% | 95.0% | 100% | 93% | 93% |
| 99.75% የደረሰ የመዝገብ የማጥራት ምጣኔ፣ | 97% | 97% | 97.25 | 97.25 % | 95.30% | 98% | 97.75 % | 97.75% | 94.9% | 97.1% | 98% | 98% | 93.8% | 95.7% | 97.7% | 94.7% | 96.9% |
| ወደ 1% የቀነሰ የመዝገብ መቋረጥ ምጣኔ | 4.23% | 4.23% | 4 | 4% | 4.60% | 87% | 3.50% | 3.50% | 4.8% | 72.9% | 3.25% | 3.25% | 5.9% | 55.1% | 3.6% | 5.1% | 70.3% |
| 99% የደረሰ በመዝገብ የማስቀጣት ምጣኔ | 92.50% | 92.50% | 95% | 95% | 91.5% | 96% | 95.25 % | 95.25% | 91.2% | 95.7% | 95.5% | 95.5% | 91.5% | 95.8% | 95.3% | 91.4% | 96.0% |
| 95% በዕርቅ ያለቁ ቀላል የወንጀል ጉዳዮች | 43.10% | 43.10% | 60% | 60% | 47.50% | 79% | 65% | 65% | 42.80% | 65.8% | 70% | 70% | 33% | 47.1% | 65% | 41.1% | 63.2% |
| 100% የተሰጠ ለጠቋሚዎችና ምስክሮች ከለላ | 80% | 80% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% |
| በመዝገብ 99% የደረሰ የዐ/ህግ ይግባኝ መዝገቦች እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | 83.20% | 83.20% | 85% | 85% | 79.8% | 94% | 87% | 87% | 76.30% | 87.7% | 89% | 89% | 73.7% | 82.8% | 87% | 76.6% | 88.0% |
| በመዝገብ ላይ 99% የደረሰ የተከሳሽ ይግባኝ መዝገቦች እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | 94% | 94% | 96% | 96% | 91.1% | 95% | 96.25 % | 96.25% | 90.8% | 94.3% | 96.50% | 96.50% | 88.2% | 91.4% | 96.25% | 90.0% | 93.5% |
| በመዝገብ 99% የደረሰ የዐ/ህግ ሰበር መዝገቦች እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | 76.60% | 76.60% | 80% | 80% | 76.10% | 95% | 82% | 82% | 65.80% | 80.2% | 84% | 84% | 67% | 79.4% | 82% | 69.5% | 84.8% |
| በመዝገብ 99% የደረሰ የተከሳሽ ሰበር እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | 90.70% | 90.70% | 93% | 93% | 84.9% | 91% | 93.50 % | 93.50% | 91.7% | 98.1% | 94% | 94% | 86.0% | 91.5% | 93.5% | 87.5% | 93.6% |
| 100% የደረሰ በሴቶች፣ ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች የመዝገብ የማጥራት ምጣኔ | 96.60% | 96.60% | 100% | 100% | 78.7% | 78.7% | 100% | 100% | 86.8% | 86.8% | 100% | 100% | 96.0% | 96.0% | 100.0% | 87.2% | 87.2% |
| ወደ 0.5% የቀነሰ በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች የመዝገብ የመቋረጥ ምጣኔ | 3.15% | 3.15% | 3% | 3% | 2.30% | 130% | 2.75% | 2.75% | 2% | 172% | 2.50% | 2.50% | 5% | 51% | 2.8% | 2.9% | 106.7% |

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ተጠሪ ተቋማት የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

| የአፈጻጸም አመልካቾች | መነሻ ዓመት 2012 | | የ2013 ዕቅድ | | የ2013 አፈፃፀም | | የ2014 ዕቅድ | | የ2014 አፈፃፀም | | የ2015 ዕቅድ | | የ2015 አፈፃፀም | | የሦስት ዓመት አማካኝ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2013 አፈጻጸም | 2013 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2014 አፈጻጸም | 2014 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2015 አፈጻጸም | 2015 አፈጻጸም በመቶኛ | የሦስት ዓመት አማካኝ ዕቅድ | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም በመቶኛ |
| በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመዝገብ 99% የደረሰ የማስቀጣት ምጣኔ | 94.60% | 94.60% | 95.50 % | 95.50 % | 95.30% | 99.8% | 96% | 96% | 97.70% | 101.8% | 96.50% | 96.50% | 91.60% | 94.9% | 96.0% | 94.9% | 98.8% |
| በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመዝገብ 99% የደረሰ የዐ/ህግ ይግባኝ እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | 96% | 96% | 96% | 96% | 85.7% | 89.3% | 96.25 | 96.25% | 100% | 103.9% | 96.75% | 96.75% | 100% | 103.4% | 96.3% | 95.2% | 98.9% |
| በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመዝገብ ላይ 99% የደረሰ የተከሳሽ ይግባኝ እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | 97% | 97% | 97% | 97% | 50% | 52% | 97.25 % | 97.25% | 50% | 51.4% | 97.50% | 97.50% | 100% | 102.6% | 97.3% | 66.7% | 68.6% |
| በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመዝገብ 99% የደረሰ የዐ/ህግ ሰበር እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | 96% | 96% | 96% | 96% | 0% | 0% | 96.25 % | 96.25% | 0.0% | 0.0% | 96.75% | 96.75% | የቀረበ የለም | | 96.3% | 0.0% | 0.0% |
| በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመዝገብ ላይ 99% የደረሰ የተከሳሽ ሰበር እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | 97% | 97% | 97% | 97% | የቀረበ የለም | | 97.25 % | 97.25% | የቀረበ የለም | | 97.50% | 97.50% | 100% | 102.6% | 97.3% | 100.0% | 102.8% |
| በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች የፍትሐብሔር ጉዳዮች የመርታት ምጣኔ | 95% | 95% | 95% | 95% | 100% | 105% | 95.50 % | 95.50% | 100% | 104.7% | 96% | 100% | 100% | 100.0% | 97% | 100.0% | 103.3% |
| የህግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን | | | 500 | 225 | 150 | 67% | 800 | 360 | 461 | 128.1% | 850 | 382 | 428 | 112.0% | 967 | 1039 | 107.4% |

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ተጠሪ ተቋማት የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

| የአፈጻጸም አመልካቾች | መነሻ ዓመት 2012 | | የ2013 ዕቅድ | | የ2013 አፈፃፀም | | የ2014 ዕቅድ | | የ2014 አፈፃፀም | | የ2015 ዕቅድ | | የ2015 አፈፃፀም | | የሦስት ዓመት አማካኝ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2013 አፈጻጸም | 2013 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2014 አፈጻጸም | 2014 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2015 አፈጻጸም | 2015 አፈጻጸም በመቶኛ | የሦስት ዓመት አማካኝ ዕቅድ | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም በመቶኛ |
| የተደረገባቸው የዐቃቤ ህግ መዝገቦች ብዛት | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የይቅርታ ተጠቃሚ የህግ ታራሚዎች ምልመላና መረጣ አፈፃፀም ጥራት ምጣኔ | 90% | 90% | 91% | 91% | 100% | 110% | 92% | 92% | 92% | 100.0% | 93% | 93% | 100% | 107.5% | 92% | 97.3% | 105.8% |
| ለህግ ታራሚዎች የተሰጠ የውሳኔ አስተያየት ጥራት ምጣኔ | 90% | 90% | 90.50 % | 90.50 % | 100% | 110% | 91% | 91% | 91% | 100.0% | 92% | 92% | 100% | 108.7% | 91% | 97.0% | 106.4% |
| በልዩ ሁኔታ የይቅርታ ተጠቃሚ የሆኑ የህግ ታራሚዎች ምጣኔ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100.0% | 100.0% |
| የታራሚዎች የአመክሮ ጥያቄ ማቅረብና ክትትል በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100.0% | 100.0% |
| በይቅርታ አሰጣጥ ፋይዳ ላይ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት በቁጥር | 1 | 1 | | | | | 1 | 1 | | | | | | | 1 | 0 | 0.0% |
| የውል ምርመራና የማጽደቅ ሽፋን ምጣኔ | | | 70% | 70% | 100% | 143% | 85% | 85% | 100% | 117.6% | 87% | 87% | 100% | 114.9% | 81% | 100.0% | 124.0% |
| 96% የደረሰ መንግስት **ከሳሽ** በሆነበት ፍትሐብሔር ጉዳዮች የመርታት ምጣኔ | 90% | 90% | 90% | 90% | 98% | 109% | 90.50 % | 90.50% | 100% | 110.5% | 91% | 91% | 100% | 109.9% | 91% | 99.3% | 109.8% |
| 96% የደረሰ መንግስት **ተከሳሽ** በሆነበት የፍትሐብሔር ጉዳይ የመርታት ምጣኔ | 90% | 90% | 90% | 90% | 94% | 104% | 90.50 % | 90.50% | 92.60% | 102.3% | 91% | 91% | 96.80% | 106.4% | 91% | 94.3% | 104.2% |
| በፍትሀብሄር ጉዳዮች የተሰጠ የህግ ምክር ሽፋን ምጣኔ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100.0% | 100.0% |
| በፍትሀብሄር አፈጻጸም ክስ 96% ገቢ የተደረገ የመንግስት ሀብት | 89% | 89% | 90% | 90% | 87.80% | 98% | 90.50 % | 90.50% | 74.30% | 82.1% | 91% | 91% | 62% | 68.1% | 91% | 74.7% | 82.5% |
| ከክስ በፊት በድርድር የተመለሰ ሀብት ምጣኔ | | | 10% | 10% | 17.90% | 179% | 11% | 11% | 7.43% | 67.5% | 12% | 12% | 14.90% | 124.2% | 11% | 13.4% | 121.9% |
| ወደ 99% ያደገ በሙስና የተመዘበረ የመንግስት ሀብትና ንብረት የማስመለስ ምጣኔ | 66.20% | 66.20% | 80% | 80% | 62.60% | 78% | 82% | 82% | 91% | 111.0% | 84% | 84% | 83.30% | 99.2% | 82% | 79% | 96% |
| ወደ 100% ያደገ በታክስ ማጭበርበር የተመዘበረ የመንግስት ሀብት የማስመለስ ምጣኔ | 95% | 95% | 95% | 95% | 54% | 57% | 95.50 % | 95.50% | 65% | 67.5% | 96% | 96% | 75.20% | 78.3% | 96% | 64.5% | 67.5% |

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ተጠሪ ተቋማት የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

| የአፈጻጸም አመልካቾች | መነሻ ዓመት 2012 | | የ2013 ዕቅድ | | የ2013 አፈፃፀም | | የ2014 ዕቅድ | | የ2014 አፈፃፀም | | የ2015 ዕቅድ | | የ2015 አፈፃፀም | | የሦስት ዓመት አማካኝ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2013 አፈጻጸም | 2013 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2014 አፈጻጸም | 2014 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2015 አፈጻጸም | 2015 አፈጻጸም በመቶኛ | የሦስት ዓመት አማካኝ ዕቅድ | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም በመቶኛ |
| 95% የደረሰ ተከሳሾች ይግባኝ የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳይ መዝገቦች ውሳኔ እንዲጸኑ የማድረግ አቅም ምጣኔ | | | 90% | 90% | 91.80% | 102% | 90.50 % | 90.50% | 100% | 110.5% | 91% | 91% | 100% | 109.9% | 91% | 97.3% | 107.5% |
| 99% የደረሰ ዓቃቤ ህግ ይግባኝ የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳይ ውጤታማነት ምጣኔ | | | 90% | 90% | 100% | 111% | 91% | 91% | 100% | 109.9% | 92% | 92% | 100% | 108.7% | 91% | 100.0% | 109.9% |
| 95% የፀና ተከሳሽ ሰበር የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳይ መዝገቦች ምጣኔ | | | 90% | 90% | የቀረበ የለም | | 90.50 % | 90.50% | 100% | 110.5% | 91% | 91% | 100% | 109.9% | 91% | 100.0% | 110.5% |
| 99% የደረሰ ዓቃቤ ህግ ሰበር የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳይ መዝገቦች ውጤታማነት ምጣኔ | | | 90% | 90% | የቀረበ የለም | | 91% | 91% | 100% | 109.9% | 92% | 92% | 100% | 108.7% | 91% | 100.0% | 109.9% |
| የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሃ-ግብር አፈፃፀም ሪፖርት ያቀረቡ ፈጻሚ ተቋማት በቁጥር | 28 | 28 | 30 | 30 | **27** | 90% | 30 | 30 | **25** | 83.3% | 30 | **30** | 0 | 0.0% | 30 | 17 | 57.8% |
| ከፈጻሚ ተቋማት በሚቀርቡ ዕቅድና አፈጻጸም ላይ የተደረገ ድጋፍና ክትትል በቁጥር | 2 | 2 | 4 | 4 | 3 | 75% | 4 | 4 | **3** | 75.0% | 4 | 4 | 0 | 0.0% | 4 | 2 | 50.0% |
| በሰብዓዊ መብት ድርጊት-መርሃ ግብር መነሻነት የተደረገ የአፈጻጸም ግምገማ መድረክ በዙር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 100% | 1 | 1 | **1** | 100.0% | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 1 | 1 | 66.7% |
| በሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ዙሪያ ለፈጻሚዎች የተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ በዙር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 100% | 1 | 1 | 1 | 100.0% | 1 | 1 | 1 | 100.0% | 1 | 1 | 100.0% |
| በሰብዓዊ መብት ህግጋት ዙሪያ ለህብረተሰቡ የተፈጠረ ግንዛቤ በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 100% | 2 | 2 | 2 | 100.0% | 2 | 2 | 1 | 50.0% | 2 | 2 | 83.3% |
| በማረፊያ ቤት በሚገኙ ተጠርጣሪዎች የተደረገ ጉብኝት በሳምንት | 98 | 98 | 104 ጊዜ | 104 | 97 | 93% | 104 | 104 | 102 | 98.1% | 104 ጊዜ | 104 | 95 | 91.3% | 104 | 98 | 94.2% |
| በማረሚያ ተቋማት በሚገኙ ታራሚዎች የተደረገ ጉብኝት በዙር | 9 | 9 | 12 ጊዜ | 12 | 10 | 83% | 12 | 12 | 11 | 91.7% | 12 ጊዜ | 12 | 9 | 75.0% | 12 | 10 | 83.3% |
| በሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጠያቂ የተደረጉ ሰዎች | | | 100% | 100% | 0% | 0% | 100% | 100% | 0% | 0.0% | 100% | 100% | 0% | 0.0% | 100% | 0% | 0.0% |

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ተጠሪ ተቋማት የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

| የአፈጻጸም አመልካቾች | መነሻ ዓመት 2012 | | የ2013 ዕቅድ | | የ2013 አፈፃፀም | | የ2014 ዕቅድ | | የ2014 አፈፃፀም | | የ2015 ዕቅድ | | የ2015 አፈፃፀም | | የሦስት ዓመት አማካኝ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2013 አፈጻጸም | 2013 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2014 አፈጻጸም | 2014 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2015 አፈጻጸም | 2015 አፈጻጸም በመቶኛ | የሦስት ዓመት አማካኝ ዕቅድ | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም በመቶኛ |
| የፀረ-ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ግብረ-ኃይል የዕቅድና ሪፖርት ግምገማ በዙር | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 100% | 2 | 2 | 2 | 100.0% | 2 | 2 | 1 | 50.0% | 2 | 2 | 83.3% |
| ለታችኛው መዋቅር ግብረ-ኃይል የተደረገ ክትትልና ድጋፍ በዙር | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 100% | 2 | 2 | 2 | 100.0% | 2 | 2 | 1 | 50.0% | 2 | 2 | 83.3% |
| በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከል ዙሪያ የተዘጋጁ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች በዙር | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 100% | 2 | 2 | 2 | 100.0% | 2 | 2 | 2 | 100.0% | 2 | 2 | 100.0% |
| የህገ-ወጥ ሰዎች ዝውውር ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የተደረጉ ጥናቶች በቁጥር | | | 1 | 1 | 0 | 0% | | | | | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 1 | 0 | 0.0% |
| ተረቀው አስተያየት የተሰጠባቸው ህጎች ምጣኔ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100.0% |
| ወደ እንግሊዘኛ የተተረጎሙ ህጎች ምጣኔ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100.0% |
| የተደረገ የህጎች ፋይዳ ጥናት በቁጥር | | | 1 | 1 | 0 | 0% | 1 | 1 | 1 | 100.0% | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 1 | 1 | 100.0% |
| ለመንግስት ተቋማት የተሰጠ የህግ ምክር አገልግሎት በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100.0% |
| የተደረገ የንቃተ ህግ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 100% | 1 | 1 | 1 | 100.0% | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 1 | 1 | 100.0% |
| የተዘጋጀ የንቃተ ህግ መፍጠሪያ ማንዋል በቁጥር | 58 | 58 | 80 | 80 | 43 | 54% | 55 | 55 | 45 | 81.8% | 60 | 60 | 25 | 41.7% | 65 | 38 | 57.9% |
| በሬድዮ/በኤሌክትሮኒክስ/ ሚዲያ የተላለፈ የንቃተ ሕግ ትምህርት ፕሮግራም ብዛት | | | | | | | 52 | 52 | 48 | 92.3% | 52 | 52 | 48 | 92.3% | 52 | 48 | 92.3% |
| በሬድዮና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ የተላለፈ የንቃተ ሕግ ትምህርት ማስተማሪያ የህግ ርዕስ ብዛት | | | | | | | 48 | 48 | 48 | 100.0% | 52 | 52 | 48 | 92.3% | 50 | 48 | 96.0% |
| በፊት ለፊት መድረክ የንቃተ ህግ ትምህርት የተሰጣቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በቁጥር | | | | | | | 1,000,000 | 450,000 | 454,543 | 101.0% | 1,050,000 | 472,500 | 376,601 | 79.7% | 461,250 | 415572 | 90.1% |
| በኤሌክትሮኒክ እና በሕትመት ሚዲያ የንቃተ ህግ ትምህርት ያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በቁጥር | 6,250,413 | 2,812,685 | 6.5 ሚሊዮን | 2,900,000 | 2,698,612 | 93% | 4.75 ሚሊዮን | 2,137,500 | 2,347,785 | 109.8% | 5 ሚሊዮን | 2,250,000 | 2,316,538 | 103.0% | 2,429,167 | 2454312 | 101.0% |
| ለታራሚዎች የተሰጠ የንቃተ ሕግ ትምህርት የወሰዱ ታራሚ ብዛት | 4567 | 2055 | 5252 | 2364 | 2,321 | 98% | 6040 | 2,718 | 2,690 | 99.0% | 6946 | 3,125 | 3,262 | 104.4% | 8207 | 8273 | 100.8% |

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ተጠሪ ተቋማት የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

| የአፈጻጸም አመልካቾች | መነሻ ዓመት 2012 | | የ2013 ዕቅድ | | የ2013 አፈፃፀም | | የ2014 ዕቅድ | | የ2014 አፈፃፀም | | የ2015 ዕቅድ | | የ2015 አፈፃፀም | | የሦስት ዓመት አማካኝ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2013 አፈጻጸም | 2013 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2014 አፈጻጸም | 2014 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2015 አፈጻጸም | 2015 አፈጻጸም በመቶኛ | የሦስት ዓመት አማካኝ ዕቅድ | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም በመቶኛ |
| ከክልሉ ዩኒቨርሲቲዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የተሰጡ ስልጠናዎች፣ | 4 | 2 | 5 | 2 | 2 | 100% | 4 | 2 | 2 | 100.0% | 5 | 3 | 0 | 0.0% | 2 | 1.3 | 57.1% |
| ተዘጋጅቶ የታተመ የንቃተ ሕግ ማስተማሪያ ቡክሌትና ብሮሸር ብዛት | 11000 | 4950 | 11,000 | 4,950 | 0 | 0% | 8,000 | 8,000 | 0 | 0.0% | 9,000 | 4,050 | 0 | 0.0% | 5667 | 0 | 0.0% |
| የተሰጡ የንቃተ ህግ ትምህርቶች ባስገኙት ፋይዳ ላይ የተደረጉ 10 ጥናቶች፣ | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0% | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 100% | 0 | 0.0% |
| የተሰበሰቡ ህግጋት በዓ/ም | 2011 | 2011 | 2012 | 2012 | 2011-2012 | 100% | 2013 | 2013 | 2013 | 100.0% | 2014 | 2014 | 2014 | 100.0% | 2011-2014 | 2011-2014 | 100.0% |
| ተጠቃለዉ ተደራሽ የተደረጉ ህጎች በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% |
| ተረጋግጠው የተመዘገቡ ሰነዶች ብዛት | 69,428 | 69,428 | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 33,512 | 100% | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 34,262 | 100.0% | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 31,996 | 100.0% | እንደ ቀረበ | 33257 | 100% |
| በተቀመጠው ስታንዳርድ የተረጋገጠ የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት ምጣኔ | 92% | 92% | 92% | 92% | 100% | 109% | 92% | 92% | 100% | 108.7% | 93% | 92.50% | 100% | 108.1% | 92% | 100% | 108.5% |
| በሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ ዙሪያ የተሰጠ ስልጠና በዙር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 100% | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 100% | 33% | 33.3% |
| በህጉ መሰረት የተሰጠ የጥብቅና ፍቃድ ብዛት | 38 | 22 | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 25 | 100% | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 40 | 100.0% | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 55 | 100.0% | እንደ ቀረበ | 120 | 100.0% |
| የታደሰ የጥብቅና ፍቃድ ብዛት | 492 | 297 | **749** | **337** | **302** | 90% | **764** | **378** | **332** | 87.8% | **561** | **302** | **278** | 92.1% | 339 | 304 | 89.7% |
| በጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ላይ በሚቀርቡ አቤቱታዎች የተሰጠ ውሳኔ ምጣኔ | 89.20% | 89.20% | 90% | 90% | 100% | 111% | 91% | 91% | 78.60% | 86.4% | 92% | 92% | 83.30% | 90.5% | 91% | 87% | 95.9% |
| በጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ላይ በሚቀርቡ ክሶች በዲስፕሊን ጉባኤ የተሰጠ ውሳኔ ምጣኔ | 89.2 | 89.2 | 90 | 90% | 64.30% | 71% | 91% | 91% | 8.30% | 9.1% | 92% | 92% | 69.50% | 75.5% | 91% | 47% | 52.1% |
| በስነ-ምግባር ጥሰት ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ጠበቆችና የግል የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ምጣኔ | 92.90% | 92.90% | 93% | 93% | 77.80% | 84% | 93.50 % | 93.50% | 100% | 107.0% | 94% | 94% | 81.20% | 86.4% | 94% | 86% | 92.3% |
| በስነ-ምግባር እና በሌሎች ርዕሶች ላይ የተሰጡ ስልጠና በዙር | 1 | 1 | 1 | 1 | 0 | 0% | 1 | 1 | 1 | 100.0% | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 1 | 0.3 | 33.3% |
| ለጠበቆችና ለህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች የተደረገ ክትትልና ድጋፍ በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 100% | 2 | 2 | 1 | 50.0% | 2 | 2 | 2 | 100.0% | 2 | 1.7 | 83.3% |

## የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ተጠሪ ተቋማት የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

| የአፈጻጸም አመልካቾች | መነሻ ዓመት 2012 | | የ2013 ዕቅድ | | የ2013 አፈፃፀም | | የ2014 ዕቅድ | | የ2014 አፈፃፀም | | የ2015 ዕቅድ | | የ2015 አፈፃፀም | | የሦስት ዓመት አማካኝ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2013 አፈጻጸም | 2013 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2014 አፈጻጸም | 2014 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2015 አፈጻጸም | 2015 አፈጻጸም በመቶኛ | የሦስት ዓመት አማካኝ ዕቅድ | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም በመቶኛ |
| ለጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች የተዘጋጁ የውይይት መድረኮች በዙር | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 100% | 4 | 4 | 1 | 25.0% | 4 | 4 | 2 | 50.0% | 4 | 2.3 | 58.3% |
| ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ያገኙ አቅም የሌላቸው ዜጎች በቁጥር | 6,212 | 3,295 | እንደቀረበ | እንደቀረበ | 893 | 100% | እንደቀረበ | እንደቀረበ | 3,681 | 100.0% | እንደቀረበ | እንደቀረበ | 4,553 | 100.0% | እንደቀረበ | 9127 | 100.0% |
| 100% ውጤታማ የሆነ ነፃ የጥብቅና አገልግሎት፣ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100.0% |
| የተዘጋጀ ክልላዊ የሲቪል ማህበራት አዋጅ በቁጥር | | | 1 | 1 | 0 | 0% | - | - | .. | | - | | | | 1 | | |
| በህጉ መሰረት የተሰጠ የሲቪክ ማሕበራት ፍቃድ በቁጥር | 49 | 26 | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 47 | 100% | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 33 | 100.0% | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 25 | 100.0% | እንደ ቀረበ | 35 | 100.0% |
| የታደሰ የሲቪክ ማሕበራት ፍቃድ በቁጥር | 82 | 45 | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 76 | 100% | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 48 | 100.0% | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | 33 | 100.0% | 52 | 52 | 100.0% |
| በማህበራት ላይ በሚቀርቡ አቤቱታዎች 100% ምላሽ ምጣኔ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100.0% |
| በሲቪክ ማህበራት ላይ የተደረገ ድጋፍና ክትትል በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 100% | 2 | 2 | 2 | 100.0% | 2 | 2 | 2 | 100.0% | 2 | 2 | 100.0% |
| የቀለም ትምህርት የተማሩ ታራሚዎች በቁጥር | 4,607 | 2,073 | 4756 | 2140 | 2126 | 99% | 4,697 | 2,113 | 2,140 | 101.3% | 4,780 | 2,151 | 2,182 | 101.4% | 2135 | 2149 | 100.7% |
| በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የሰለጠኑ ታራሚዎ በቁጥር | 5,700 | 2,565 | 6680 | 3006 | 3,094 | 103% | 2,500 | 1,125 | 1,125 | 100.0% | 2,531 | 1,138 | 1,327 | 116.6% | 1756 | 1849 | 105.3% |
| የተገነባ ዘመናዊ የግብርና እና የዕደ ጥበብ ማዕከላት በቁጥር | | | | | | | | | .. | | 1 | 1 | | | 1 | 0 | 0.0% |
| የሥነ ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርት የሰለጠኑ ታራሚዎች በቁጥር | 6,207 | 2,795 | 6,388 | 2,875 | 3,170 | 110% | 6886 | 3,098 | 2,700 | 87.2% | 6,919 | 3,113 | 3,207 | 103.0% | 3029 | 3026 | 99.9% |
| የምክክር አገልግሎት ያገኙ ታራሚዎች በቁጥር | 6,861 | 3,087 | 6500 | 2,925 | 2,805 | 96% | 6,450 | 2,902 | 2,682 | 92.4% | 6,968 | 3,135 | 2,960 | 2,960 | 2987 | 2816 | 94.3% |
| የኮ-ካውንስለር ስልጠና ያገኙ ታራሚዎች በቁጥር | | | 200 | 90 | 78 | 87% | 200 | 90 | 79 | 87.8% | | | | | 60 | 52 | 87.2% |
| የተቋቋመ የወጣት ጥፋተኞች የተሀድሶ ማዕከል በቁጥር | | | | | | | | | .. | | 1 | 1 | | 0.0% | 1 | 0 | 0.0% |
| በሚኒማ መሠረት የቀረበ የምግብ አቅርቦት በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% |
| የተሟላ የመጠጥና የንጽህና መጠበቂያ ውሃ አቅርቦት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% |

# የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ፍትህ ቢሮ እና ተጠሪ ተቋማት የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ

| የአፈጻጸም አመልካቾች | መነሻ ዓመት 2012 | | የ2013 ዕቅድ | | የ2013 አፈፃፀም | | የ2014 ዕቅድ | | የ2014 አፈፃፀም | | የ2015 ዕቅድ | | የ2015 አፈፃፀም | | የሦስት ዓመት አማካኝ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2013 አፈጻጸም | 2013 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2014 አፈጻጸም | 2014 አፈጻጸም በመቶኛ | ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/ | የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ድርሻ | 2015 አፈጻጸም | 2015 አፈጻጸም በመቶኛ | የሦስት ዓመት አማካኝ ዕቅድ | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም | የሦስት ዓመት አማካኝ አፈጻጸም በመቶኛ |
| በመቶኛ | | | | | | | | | | | | | | | | | |
| የጤና አገልግሎት ያገኙ የህግ ታራሚዎች በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% |
| የተሟላ የህግ ታራሚዎች የመዝናኛ ክበባት በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% |
| የተቋቋመ የሥነ-አእምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል በቁጥር | | | | | | | | | .. | | 1 | | | | | | |
| አዲስ የተገነባ የታራሚዎች መጠለያ በቁጥር | 11 | 3 | 2 | 0 | | | | | .. | | 2 | | | | | | |
| የተጠናከረ የጥበቃና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% |
| የተቋሙ ዓላማ፣ ደንብና መመሪያ ያወቁ ታራሚዎች በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% |
| የተያዙ የተከለከሉ ቁሳቁሶች በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% |
| የተሃድሶ ስልጠና የወሰዱ አባሎች በቁጥር | | | 100 | 45 | 53 | 118% | 100 | 45 | 43 | 95.6% | 100 | 45 | 0 | 0.0% | 135 | 96 | 71.1% |
| አዲስ የሰለጠኑ ምልምል ፖሊሶች በቁጥር | 248 | 115 | 254 | 120 | 102 | 85% | 254 | 120 | 133 | 110.8% | 254 | 133 | 0 | 0.0% | 373 | 235 | 63.0% |
| የቅድመ ሥራ ስልጠና የሰለጠኑ የህግ ባለሙያዎች በቁጥር | 109 | 52 | 130 | 65 | 60 | 92% | 134 | 65 | 60 | 92.3% | 141 | 65 | 60 | 92.3% | 195 | 180 | 92.3% |
| የሥራ ላይ ስልጠና የሰለጠኑ የህግ ባለሙያዎች በቁጥር | 132 | 60 | 124 | 55 | 56 | 102% | 130 | 60 | 80 | 133.3% | 130 | 60 | | | 175 | 136 | 77.7% |
| አጫጭር ስልጣና የሰለጠኑ የህግ ባለሙያዎች በቁጥር | 538 | 245 | 858 | 386 | 354 | 92% | 1000 | 450 | 438 | 97.3% | 1000 | 450 | 259 | 57.6% | 429 | 350 | 81.7% |
| የተደረገ የስልጠና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 100% | 1 | 1 | 1 | 100.0% | 1 | | | | 1 | 1 | 100.0% |
| የምርምር ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 100% | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 1 | 1 | 1 | 100.0% | 1 | 0.7 | 66.7% |
| በተመረጡ ህጎች ላይ የተደረገ ጥናት | 6 | 6 | 7 | 7 | 6 | 86% | 7 | 7 | 0 | 0.0% | 7 | 7 | 5 | 71.4% | 7 | 4 | 52.4% |
| በፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም ዙሪያ የተሰጠ የማማከር አገልግሎት በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100% | 100.0% | 100% | 100% | 100.0% |
| የተዘጋጀ ክልል አቀፍ የፍትህ ሳምንት በዙር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 100% | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 1 | 1 | 0 | 0.0% | 1 | 0.3 | 33.3% |
| በፍትህ ዘርፉ የሚከናወኑ የማሻሻያ ፕሮግራሞች አፈጻጸም ዙሪያ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ በዙር | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 100% | 4 | 4 | 4 | 100.0% | 4 | 2 | 0 | 0.0% | 3 | 2.7 | 80.0% |
| የተደረገ የፍትህ ተቋማት ጥምረት መድረክ በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 100% | 2 | 2 | 1 | 50.0% | 2 | 2 | 1 | 50.0% | 2 | 1.3 | 66.7% |
| የተሰበሰበ፣ የተተነተነና የተደራጀ የፍትህ መረጃ ምጣኔ | | | | | | | 60% | 60% | 40% | 66.7% | 70% | 70% | 45% | 64.3% | 65% | 43% | 65.4% |

# ክፍል ሁለት
# ተቋማዊ ዳሰሳ

## 2.1 የተቋማቱ ተግባርና ኃላፊነት *(በነባሩ ክልል)*

### 2.1.1 የፍትህ ቢሮ ስልጣንና ተግባር

የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የክልሉ ፍትህ ቢሮ እና ተጠሪ ተቋማት መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 177/2011 እና የክልሉ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 178/2011 ላይ ለተቋሙ የተሰጡ ዋና ዋና ስልጣንና ተግባራት፤

- በሕግ ጉዳዮች የክልል መንግስት ዋና አማካሪ እና ተወካይ ሆኖ መስራት፣
- በፌደራል መንግስት ተዘጋጅቶ የጸደቀውን የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆን ማስተባበር፣ መከታተልና ማረጋገጥ፣
- የወንጀል ፍትሕ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተንና ማሰራጨት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትና ማስፈጸም፣
- በፌዴራልና በክልሉ ሕገ-መንግስታት እና በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ የግልና የቡድን መሰረታዊ መብቶች እና ነፃነቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ፣
- በክልሉ ፍርድ ቤት ስልጣን ስር በሚወድቁ በማናቸውም የፀረ-ሙስና እና የታክስ ህጎችን በመጣስ በሚፈፀሙ የወንጀል ጉዳዮች እንዲሁም ከባድና ውስብስብ በሆኑ ሌሎች የወንጀል ድርጊቶች የወንጀል ምርመራ ከፖሊስ ጋር አብሮ ማጣራት፣ ምርመራውን በበላይነት መምራት፣
- በሕዝብ ጥቅም መነሻ ወይም በወንጀል የማያስጠይቅ ሁኔታ መኖሩ በግልፅ ሲታወቅ የወንጀል ምርመራ እንዲቋረጥ ወይም የተቋረጠው የወንጀል ምርመራ እንዲቀጥል ማድረግ፤ ማናቸውም የወንጀል ምርመራዎች በሕግ መሰረት መከናወናቸውን ማረጋገጥ፤ አስፈላጊውን ህጋዊ ትእዛዝ ለሚመለከተው አካል መስጠት፣
- ምርመራቸው በፖሊስ በተጀመረባቸው መካከለኛ፣ ቀላል እና በግል አቤቱታ በሚቀርቡ የወንጀል ጉዳዮች ምርመራ በአግባቡ ስለመከናወኑ በቅርበት ክትትል ማድረግ፤ በተጀመረ የወንጀል ምርመራ አስመልክቶ ፖሊስ ለዓቃቤ ህግ ማሳወቁን ማረጋገጥ፣
- በወንጀል መዝገብ ላይ የተሰጠ የዓቃቤ ሕግና የፍርድ ቤት ውሳኔዎችን ለሚመለከተው ፖሊስ ማሳወቅ፣ የወንጀል ምርመራ መዝገቦችን አስመልክቶ በየደረጃው ባሉ ዓቃቤያነ ሕግ በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ በፖሊስ የሚቀርቡ አቤቱታ ተቀብሎ ውሳኔ መስጠት፤
- የተጠናቀቁ የምርመራ መዝገቦችን ከሕግና ከማስረጃ አንፃር መርምሮ በሕግ የተቀመጡ መመዘኛዎች ሲሟሉ የአያስከስስም ወይም የተዘግቷል ውሳኔ መስጠት፤
- የጥፋተኝነት ድርድር ይወስናል፣ ድርድር ያደርጋል፣ አማራጭ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ መወሰን፣ ተግባራዊነቱን መከታተል፤

- መንግስትን በመወከል የወንጀል ጉዳዩች ክስ ይመሰረታል፣ ይከራከራል፣ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ክስ ማንሳት፣ የተነሳ ክስ እንዲቀጥል ማድረግ፣
- የወንጀል ድርጊት ጠቋሚዎችና ምስክሮች በህግ መሰረት ጥበቃና ከለላ እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በማረፊያ ቤትና  በማረሚያ ቤት ቁጥጥር ሥር ያሉ ተጠሪጣሪዎችንና ታራሚዎችን መጎብኘት፣ አያያዛቸው እና ቆይታቸው በሕግ መሰረት መፈጸሙን ማረጋገጥ፣ ሕገ ወጥ ተግባር ተፈፅሞ እንደሆነ እንዲታረም ማድረግና ሕግን ተላልፈዋል በተባሉ ሰዎች ላይ በሕግ መሰረት እርምጃ መውሰድ ወይም እንዲወሰድ ማድረግ፤
- በዕርቅ ሊያልቁ የሚችሉ የወንጀል ድርጊቶች በእርቅ የሚጠናቀቁበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- ፍ/ቤቶች በወንጀል ጉዳይ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና ትዕዛዞች መፈፀማቸውና መከበራቸውን መከታተል፣ ሳይፈፀሙ ከቀሩ ወይም አፈፃፀማቸው ሕግን ያልተከተለ ከሆነ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ለሰጠው ፍ/ቤት በማመልከት የዕርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ፤
- በፍርድ ቤት የሚወሰኑ የወንጀል ቅጣቶች በአግባቡ እንዲፈፀሙ ለማድረግ የሚያስችሉ ሥርዓቶችን ማደራጀት ወይም መደራጀታቸውን ማረጋገጥ፣
- የሞት ቅጣት ውሳኔዎችን ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት በፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ በኩል እንዲቀርብ ማድረግ፣ አፈፃፀሙን መከታተል፣
- በክልል የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሕዝብ እና የክልል መንግስት መብትና ጥቅም ወኪል ሆኖ መከራከር፣ ማስከበር፣ እንዲከበሩ ማድረግ፣ የሚከበሩበትን ሂደት መከታተል፣ መቆጣጠር፣
- ትላልቅ የመንግስት ፕሮጀክቶችን የውል ዝግጅት እና ድርድር ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማድረግ፣ የሕዝብና የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶች ጥቅም ይጎዳል ብሎ ሲያምን በሌሎች ጉዳዮች ውል እና የመግባቢያ ሰነዶች ዝግጅትና ድርድር ማድረግ ወይም የሚመለከታቸውን አካላት ማማከር፣
- የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶችን በመወከል የፍትሐብሔር ክስ መመስረት፤ በከሰሱበት ወይም በተከሰሱበት የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ክርክር ማድረግ፤ በተጀመረ ክርክር ተቋማትን ተክቶ በተናጠል ወይም በጋራ መከራከር፣ ወይም በክርክር አመራር ላይ ለመሥሪያ ቤቶች አቅጣጫ መስጠት፣ በሕግ መሠረት ለተሰጡ ውሳኔዎች ፍርድን ማስፈጸም፤
- በክልሉ መንግስት መስሪያ ቤቶች እና በግል ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች መካከል የሚከሰቱ የፍትሐብሔር ክርክሮች በድርድር እንዲያልቁ ጥረት ማድረግ፣ ድርድሩ ካልተሳካ ጉዳዩን ስልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍርድ ቤት አቅርቦ መከራከር፣
- የክልል መንግስት መስሪያ ቤቶች እርስ በርሳቸው ያልተግባቡባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዩች በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጭ ባለ አማራጭ የክርክር መፍቻ መንገድ እንዲወሰን ውሳኔ ሀሳብ መስጠት፣ በውሳኔው መሰረት መፈፀሙን ማረጋገጥ፤
- የተመዘበረ የመንግስት ገንዘብ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ክስ በማቅረብ ማስመለስ፣ የሙስና ወንጀል ውጤት የሆኑት እና በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ንብረቶችን ማስተዳደር፤ እንዲወረስ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶች ለሚመለከተው የመንግስት አካል ማስተላለፍ፣

- የፍትሐብሔር ክስ ለመመሥረት የገንዘብ አቅም የሌላቸውን ዜጎች በተለይም ሴቶችን፣ ሕፃናትን፣ አካል ጉዳተኞችን እና አረጋውያንን ወክሎ መከራከር፤
- የገንዘብ አቅም የሌላቸው የወንጀል ተጎጂ የሆኑ ተበዳዩች እንዲካሱ መልሰው እንዲቋቋሙ እንዲሁም ከጉዳቱ የተያያዙ የፍትሐብሔር ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ እነሱን በመወከል የፍትሐብሔር ክስ ማቅረብ ወይም መደራደር፤
- በክልል መንግሥት የሚወጡ ሕጎች የሕግ ረቂቅ ዝግጅት ስራ መስራት፤ የመንግስት አካላት የሚያዘጋጁት ረቂቅ ህግ ከፌዴራልና ከክልሉ ሕገ መንግስትና ከሌሎች ሕጎች ጋር የተጣጣመ መሆኑን ማረጋገጥ፣ ለሚመለከታቸው ክፍሎችም አስተያየት ማቅረብ፤
- በክልሉ በስራ ላይ ባሉ ህጎች ጥናት በማድረግ ሕጎች እንዲሻሻሉ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣ ሲደገፍም ለተባሉት ማሻሻያዎች ረቂቆችን በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ፣
- ሕጎችን የማሰባሰብ፣ የማጠቃለልና የኮዲፊኬሽን ሥራ ይሰራል፤ የክልሉን ህጎች በባለአደራነት መያዝ፣ ማሰራጨት፤
- ዓቃቤያነ ሕግ ስለ ስራቸው ያላቸውን አመለካከት፣ እውቀትና ክህሎት  በተከታታይ እና በየደረጃው ለማሳደግ ትምህርት እና ሥልጠና መስጠት ወይም እንዲሰጣቸው ማድረግ፤
- የህብረተሰቡን ንቃተ ሕግ ለማዳበር ለክልሉ ህብረተሰብ በተለያዩ ዜደዎች የንቃተ ህግ ትምህርት መስጠት፣
- በክልሉ ፍርድ ቤቶች ለሚከራከሩ ጠበቆች ፈቃድ መስጠት፣ ማደስ፣ ስራቸውን መቆጣጠር፣ የጠበቆችን ዲሲፕሊን ጉዳዮች አይቶ መወሰን፤ በህግ መሰረት መሰረዝ፣
- በክልሉ የሚንቀሳቀሱ የኢትዮጵያውያን የበጎ አድራጎት ድርጅቶችንና ማህበራትን መመዝገብ፣ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት መስጠት፣ ስራቸውን መቆጣጠር፣ ማረጋገጥ እና በሕግ  መሰረት መሰረዝ፣
- አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሰነዶችን መመዝገብ፣ ማረጋገጥ፣  መሻር፣ መሰረዝ፣
- ነፃ የሕግ ድጋፍ አሰጣጥ ስትራቴጂዎችን መቅረጽ፣ አፈፃፀሙን መከታተል፣ በመስኩ የሚሰማሩ አካላትን ማስተባበር፣
- ብሄራዊ የሰብአዊ መብት ድርጊት መርሀግብር መነሻ በማድረግ ክልላዊ ሰብአዊ መብት የድርጊት መርሀ ግብርን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ማዘጋጀት፣ አፈፃፀሙን መከታተል፤ በክልል ደረጃ የሚመለከታቸውን አካላት ማስተባበር፣ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ማቅረብ፣
- የዓቃቤ ሕግ የውሳኔ አሰጣጥ እና የፍቅደ ሥልጣን አጠቃቀም ወጥነትን ለማረጋገጥ በጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ የፀደቀ መመሪያ ተግባራዊ መደረጉን ማረጋገጥ፣
- በዓቃቤያነ ሕግ የሚሰጡ ውሳኔዎች በሕግ መሰረት መከናወናቸውን የሚያረጋግጥ  የኢንስፔክሽን ክፍል ማደራጀት፣ ጉድለቶችን በጥናት አስደግፎ መለየት፤ በግኝቱ መሠረትም እንዲታረሙ ማድረግ፣ አስፈላጊ ሲሆን እርምጃ መውሰድ ወይም እንዲወሰድ ማድረግ እና መልካም ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት፣
- የክልሉን ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ኮሚሽን ሥራዎች በበላይነት መምራት፣ መከታተል፣ ማስተባበር፤ የህግ ታራሚዎች ይቅርታ የሚያገኙበትን ስርዓት መዘርጋት፣

### 2.1.2 የማረሚያ ኮሚሽን ተግባርና ኃላፊነት

ማረሚ ኮሚሽኑ በአዲሱ ተቋማዊ ሪፎርም መሠረት ተጠሪነቱ ለክልሉ ፍትህ ቢሮ ተጠሪ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የመሠረታዊ አሠራር የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት መሠረት በአዲስ መልክ በአራት ዳይሬክቶሬት ማለትም ፡-

1. የታራሚዎች ማረምና ማነጽ ዳይሬክቶሬት
2. የጥበቃ ደህንነትና የታራሚዎች አስተዳደር ዳይሬክቶሬት
3. የመሠረታዊ ፍላጎት አቅርቦት ዳይሬክቶሬት
4. የበሽታ መከላከልና የፈውስ ሕክምና አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ተደራጅቷል፡፡ የኮሚሽኑን ዝርዝር ስልጣንና ተግባራትን ስንመለከት፡-

1) በፍርድ ቤቶች ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መሠረት ወደ ማረሚያ ተቋማት የሚላኩትን የሕግ ታራሚዎች ይቀበላል፤ይጠብቃል፤ ያርማል እንዲሁም ከፍርድ ቤት የሚሰጡ ሌሎች ትዕዛዞችን ይፈጽማል ወይም እንዲፈፅሙ ያደርጋል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤
2) የታራሚዎችንና የቀጠሮ እስረኞችን ጤንነት እንዲጠበቅ ያደርጋል፡፡ በሚወጣው ደንብ መሠረት ታራሚዎች እና የቀጠሮ እስረኞች ነፃ ሕክምና፣ ምግብና መጠለያና የአልባሳት አግልግሎቶችን እንዲያገኙ ያደርጋል፤
3) ታራሚዎች ከተፈቱ በኋላ ራሳቸውን ለማስተዳደር የሚችሉና ለሕግ ተገዥ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል የቀለም ትምህርት፣ የሙያ ሥልጠና፣የምክር አገልግሎት፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎት እንዲሁም በገቢ ማስገኛ ሥራዎች ተደራጅተው በመስራት ገቢ እንዲያገኙ ያደርጋል፤
4) የህግ ታራሚዎች እና የቀጠሮ እስረኞች በማረሚያ ተቋም ቆይታቸው ጊዜ የማረሚያ ተቋም መተዳደሪያ ደንብና መመሪያን በመጣስ ለሚፈፅሙት ጥፋት በወጣው ደንብ ወይንም መመሪያ መሠረት የሥነ-ሥርዓት ቅጣቶች እንዲወሰን ያደርጋል፤ አፈፅፀሙንም ይከታተላል፤
5) በክልል አቀፍ ደረጃ የህግ ታራሚዎች እና የቀጠሮ እስረኞች መረጃዎችን እና ስታስቲክሶችን ያሰባስባል፣ ያጠናቅራል፣ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያደርጋል፤
6) ታራሚዎች በሚያሳዩት የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ በሕግ መሠረት በአመክሮ እና በይቅርታ እንዲፈቱ ሥልጣን ለተሰጠው አካል ጥያቄ እንዲቀርብ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
7) በሥሩ የሚገኙ ማረሚያ ተቋማትን ያስተዳድራል፣ ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤ እንዲሁም የማረሚያ ተቋማት ኃላፊዎችን ይመድባል፡፡
8) ኮሚሽኑ ለሥራ አስፈላጊ የሆኑ የማረሚያ ምልምል ፖሊስ አባላት በመስፈርቱ መሠረት ይመለምላል፣ ያሠለጥናል ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ የሲቪል ሠራተኞችንና የፖሊስ አባላትን የሙያ ብቃት ለማሳደግ የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፤
9) የታራሚዎች እና የቀጠሮ እስረኞችን አጠባበቅና አያያዝ ለማሻሻልና የማረሚያ ፖሊስ አባላትን የሙያ ብቃትና አገልግሎት በክልል ደረጃ ተመሳሳይነት ያለውና ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ የሚረዱ ጥናቶችን ያጠናል፣ ማንዋሎችን ያዘጋጃል፤
10) ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ማረሚያ ተቋማት ትኩረት በመስጠት የትምህርት፣ የሙያ ስልጠና፣ የቴክኒክና የምክር ድጋፍ ይሰጣል፣
11) ኮሚሽኑን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ከፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደርና ከተለያዩ ክልል ማረሚያ ኮሚሽኖች እና አግባብ ካላቸው መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፣ በቅንጅት ይሰራል፤
12) የማረሚያ ፖሊስ አባሎችና ቤተሰቦች የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤
13) ለማረሚያ ተቋማት አገልግሎት የሚውሉ አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎችን ከክልል መንግስትና ከፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ጋር በመተባበር እንዲሟላ ያደርጋል፤

14) ለኮሚሽኑ አባላት የሚያገለግል የደመወዝ እስኬልና ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን አጥንቶ ለመንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል
15) ለኮሚሽኑ የሚያገለግሉ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችንና የስፖርት ማበልፀጊያ ማዕከል ያቋቁማል፤
16) የኮሚሽኑን የስትራቴጂክ ዕቅድ መሠረት በማድረግ የረዥም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ዕቅዶችን ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
17) በክልሉ የሚገኙ የማረሚያ ፖሊስ አባላት የማዕረግ ዕድገት ዝውውርና የአለባበስ መመዘኛዎች ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅም ባለው ሕግና ደንብ መሠረት መፈፀሙን ይከታተላል፤
18) የወጣት ጥፋተኞችን ተሃድሶ ማዕከል እንዲቋቋም ያደርጋል፣ በበላይነት ይመራል ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር ወጣት ጥፋተኞች የቀለምና የሙያ ትምህርት አግኝተው አምራችና መልካም ዜጋ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡
19) የወቅቱን የገበያ ሁኔታ በማጥናት ለህግ ታራሚዎች የሚመደበው የምግብና የህክምና በጀት እንዲሻሻል ጥናት በማድረግ ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤
20) በክልሉ የታራሚዎች የልማት ማዕከል እንዲቋቋም ያደርጋል፤
21) በሌሎች ህጎችና ድንጋጌዎች ለኮሚሽኑ የተሰጡ ስልጣንና ተግባሮችን በሥራ ላይ ያውላል፤ሊሻሻሉ የሚገቡ ደንቦችን በመለየት ማሻሻያ እንዲደረግባቸው ለሚመለከተው ክፍል/አካል ያቀርባል
22) ውል ይዋዋላል፣ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ በራሱም ስም ይከሳል፤ ይከሰሳል፤
ዓላማውን ለመፈፀም የሚረዱ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

### 2.1.3 የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠናና የህግ ምርመር ማዕከል ተግባርና ኃላፊነት

ማዕከሉ በአዋጅ ቁጥር 113/99ዓ.ም የተቋቋመ ሲሆን በዚህ አዋጅ መሰረት ከተሰጡት ሰልጣንና ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ፡- በክልሉ ፍትህ አካላት ውስጥ በዳኝነት፣በዐ/ህግነት፣በተከላካይ ጠበቃነት ወይም በሌሎች ከፍትህ ስርዓቱ ጋር ተዛማጅነት ካላቸው ሙያዎቸ ውስጥ የፍትህ ስርዓቱን ለሚቀላቀሉ ህግ ባለሙያዎች ቅድመ ስራ ስልጠና፣ለተቀላቀሉት የሙያ ብቃታቸውን ከፍ ለማድረግ በሚያስችላቸው ጉዳዮችዙሪያ ቀጣይነት ያላቸውን የስራላይና አጫጭር ስልጠና መስጠት፣ በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ ለሚታዩ የተዘበራረቁ የፍትህ ስርዓት አሰራሮች ተስተካክለው ወጥነት እንዲኖራቸው ደረጃቸውን የጠበቁ የፍትህ አሰጣጥ ስርዓቶች በሁሉም ቦታ እውን እንዲሆንኑ ተገቢውን የህግ ጥናት ምርምር በማድረግ የውሳኔ ሃሳብ ማመንጨት፣ከሌሎች አካላት ጋር በመቀናጀት የፍትህ ስርዓቱ መጠንከር አስተዋጽኦ በሚኖራቸው የፍትህ ማሻሻያ ጉዳዮች ላይ የመደገፍ፣የመከታተል፣ማማከርና የማስተባበር፣ የፍትህ መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግና የመረጃ ማዕከል ሆኖ የማገልገል ሃላፊነቶች ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

## 2.2 የተቋማቱ ማስፈፀሚያ ተቋማዊ አቅም፣ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች

### 2.2.1 የሕገ መንግስት፣ ሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነዶች ቅኝት፣

የክልሉ ፍትህ ቢሮ፣ የማረሚያ ኮሚሽን፣ የፍትህ አካላት ባለሙያዎች ስልጠናና የህግ ምርምር ማዕከል የቀጣይ የ7 ዓመቱን መሪ የልማት ዕቅድ ለማቀድ በመነሻነት ለመውሰድ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ እና የክልላችን ህግጋተ መንግስት፣ ሀገራዊ የፖሊሲ እና የስትራቴጅ ሰነዶችን ለመቃኘት ጥረት ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት የኢ.ፌ.ዲ.ሪ እና የክልላችን ህግጋተ መንግሥት፣ የኢትዮጵያ የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጉዳዮች፣ የማስፈፀም አቅም ግንባታ፣ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂዎች የሴቶች ጉዳይ፣ የህጻናት፣ የወጣቶች ጉዳይ፣ የአካባቢ ጥበቃ ወይም የአረንጓዴ ልማት፣ የማህበራዊ ጥበቃ፣ የወንጀል ፍትሕ

ፖሊሲዎች እና የፍትሕ ሥርዓት ማሻሻያ ፕሮግራም ከተቋሙ ተግባርና ኃላፊነት ጋር ካላቸው ግንኙነት አንጻር ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

## የሕገ መንግስት፣ ሀገራዊ ፖሊሲና ስትራቴጂ ሰነዶች ቅኝት፤

| ተ.ቁ | የፖሊሲ፣ የህግ እና የስትራቴጂ ጉዳዮች | የፖሊሲ አቅጣጫዎች /የትኩረት ነጥቦች/ | ከተቋማቱ ጋር ያለው ቁርኝት /ግንኙነት/ ወይም ከተቋማቱ የሚጠበቅ |
|---|---|---|---|
| መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ በመተግበሩ እና ክለሳ ተደርጎ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት ጅምር መኖሩ፣ | ➢ ከትግበራ እና ከክለሳው በኋላ የተገኙትን መልካም ተሞክሮዎች በመቀመርና በማስፋፋት እንዲሁም ቀጣይት እንዲኖራቸው በማድረግ፣<br>➢ ስራን ማዕከል ያደረገ ግልጽ የሆነ ተቋማዊ አደረጃጀትና አሰራር በመዘርጋት፣<br>➢ የተቀናጀ አመራር ሥርዓትና ጠንካራ የቡድን ሥራ በሚፈለገው ደረጃ በማድረስ፣<br>➢ የአገልግሎት አሰጣጣችን ተገልጋይ ተኮር፣ ጥራት ያለው፣ የተቀላጠፈና ውጤታማ እንዲሆን ማድረግ፣<br>➢ አገልግሎት አሰጣጡ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ፣ ተደራሽና ህብረተሰቡን የሚያሳትፍ በማድረግ፣<br>➢ ለሚነሱ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች በአጭር ጊዜ ውሳኔ በመስጠት፣<br>➢ የፈፃሚውን የአገልጋይነት ስሜት እንዲሻሻል በማድረግ፣<br>➢ የማትጊያ ስርዓት ተግባራዊ በማድረግ፣ |
| የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱን መሠረት ያደረገ ውጤት ተኮር ዕቅድ እየተዘጋጀ መተግበሩ፣ | ➢ ሥራን በዕቅድ በመምራት፣<br>➢ የክትትልና ግምገማ አሰራሩ በጥራትና በውጤት ላይ ያተኮረ እንዲሆን በማድረግ፣<br>➢ ስትራቴጂካዊ ጉዳዮችን ትኩረት ሰጥቶ በመስራት፣<br>➢ ተቋሙ በዕቅድ ዘመኑ ሊያሳካቸው የሚገቡ ዋና ዋና ጉዳዮችን ትኩረት ሰጥቶ በመሥራት፣ |
| ከክልልና ከፌዴራል ፍትሕ አካላት ጋር በቅንጅት መሥራት፣ | ➢ የጋራ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተከታታይነት ያለው መድረክ በመፍጠር፣<br>➢ የተጀመሩ የቅንጅት ስራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል፣<br>➢ መልካም ተሞክሮዎችን አጠናክሮ ለማስቀጠል የሚያስችሉ የልምድ ልውውጥ በማድረግ፣ |
| በጀትና ዕቅድን ያስተሳሰረ ሥርዓት መዘርጋቱ፣ | ➢ ውጤት ከበጀት ጋር እንዲተሳሰር በማድረግ አፈፃፀምን በውጤት በመለካት፣<br>➢ በዕቅድ የተመራ የፋይናንስ አጠቃቀም በማስፈን፣<br>➢ ለቁልፍ ሥራዎች ቅድሚያ በመስጠት፣<br>➢ ውጤታማ የበጀት አጠቃቀምን በማስፈን፣<br>➢ ዕቅድን መሠረት ያደረገ የበጀት እጥረትን ለመሸፈን የሚያስችል የሀብት ማፈላለግ ሥራን አጠናክሮ በመሥራት፣ |
| የማስፈፀም አቅም መሻሻል መጀመሩ፣ | ➢ የተቋሙን ራዕይና ተልእኮ የሚያሳኩ ተከታታይነት ያለው የአጭርና የረዥም ጊዜ ስልጠናዎችን በመስጠት፣<br>➢ ተቋሙን በሰለጠነና ብቃት ባለው የሰው ሃይል በማሟላት፣<br>➢ በየደረጃው ያለው አመራርና ፈጻሚ የማስፈፀም አቅሙን በማጎልበት፣<br>➢ የሰራተኛው አፈፃፀም ውጤታማነት በመለካት፣<br>➢ እቅድን በለውጥ መሳሪያ ደግፎ መተግበር፣ |
| በቡድን የመሥራት ልምድ እየዳበረ መምጣቱና የሠራተኛው የአገልጋይነት ስሜት መዳበሩ፣ | ➢ ተተካክቶ በመስራት፣<br>➢ ስራን ማዕከል ያደረገ ግምገማዎችን በማካሄድ፣<br>➢ እርስ በእርስ በመማማር፣ |

| አስቻይ ሁኔታዎች | አስቻይ ሁኔታዎችን እንዴት እንጠቀምባቸው? |
|---|---|
| በክልሉና በሀገሪቱ እየተመዘገበ ያለ ተከታታይ የኢኮኖሚ ዕድገት መኖሩ፣ | ➢ በሕብረተሰቡ ዘንድ ልማታዊ አስተሳሰብ እንዲሰርፅና ወንጀል እንዲቀንስ በማድረግ፣<br>➢ የክልሉን የአገሪቱ ዕድገት ያስገኘውን እና ያመጣውን አዎንታዊ ለውጥ የተቋሙን ተልዕኮ ለማሳካት በመጠቀም፣<br>➢ ልማታዊ ባለሀብቱን አጋር አድርጎ በመሥራት፣ |
| ለፍትሕ ስርዓቱ ግንባታ ለጋሽ ድርጅቶች የሚያደርጓቸው ድጋፎች መኖራቸው፣ | ➢ የክልሉን ጥቅምና ለፍትሕ ስርዓቱ ያለውን አጋዥነት ቅድምያ ሰጥቶ በመለየት ለጋሽ ድርጅቶች ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ በመቀጠል፣<br>➢ ለተቋማቱ ተልእኮ ማስፈፀሚያ የሚረዱ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርፆ ሃብት በማፈላለግ ተቋሙን ማደራጀት፣ |
| በክልሉ የፍትህ  ተቋማት መስፋፋታቸው፣ | ➢ በፍትህና በህግ ነክ ጉዳዮች ላይ በጋራ በመስራት፣<br>➢ የተቋማትን ፈፃሚዎችንና አመራሮችን አቅም እንዲጎለብት በማድረግ፣<br>➢ ነፃ የህግ ድጋፍ ለህብረተሰቡ እንዲሰጡ በማድረግ፣<br>➢ የተቋማትንን ራዕይና ተልእኮ ሊያሳኩ የሚችሉ ባለሙያዎችን በጥራትና በመጠን በማዘጋጀትና በማቅረብ፣ |
| የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን መስፋፋትና የዘመናዊ አሰራር እያደገ መምጣቱ፣ | ➢ የቴክኖሎጂ አቅርቦትንና አጠቃቀምን  በማስፋፋት፣<br>➢ አገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ፣<br>➢ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም የፈፃሚውን አቅም በማሳደግ፣ |
| የብዙኃን ማህበራት ለፍትህ ስርዓቱ አጋዥ መሆናቸው እና ህብረተሰቡን አሳታፊ የሆነ አሰራር መጀመሩ፤ | ➢ ህዝቡ የፍትህ ጉዳይ የኔ ጉዳይ ነው የሚል አስተሳሰብ እንዲይዝ ለማድረግ የሚያስችል ግንዛቤ በመፍጠር፣ ለፍትህ ስርዓቱ አጋዥ እንዲሆን በማድረግ፣<br>➢ ሕዝቡ በተደራጀ መልኩ የፍትህ ስርዓቱን እንዲገመግም እና ግብዓት እንዲሰጥ በማስቻል፣ |
| ያለተማከለ አስተዳደር መኖር፣ | ➢ በየደረጃው ተዋቀረውን የአስተዳደር እርከን በመጠቀም የፍትህ ተደራሽነትን በማረጋገጥ እና የመረጃ ልውውጥ ስርዓትን በማጠናከር፣ |
| የብዙሃን መገናኛ መስፋፋት እና ለፍትህ ስርዓቱ አጋዥ እየሆኑ መምጣታቸው ፣ | ➢ ህብረተሰቡ የህግ ግንዛቤ እንዲያገኝባቸው በማድረግ፣ |
| አንጻራዊ ሠላም መኖር | ➢ ተቋማትን ተልዕኮውን በአግባቡ እንዲወጣ በማድረግ፡፡ |

◈ ***ፈታኝ ሁኔታዎች፤***

| ፈታኝ ሁኔታዎች | የመፍትሔ እርምጃዎች |
|---|---|
| ከስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ይልቅ በደራሽ ጉዳዮች (በድርጅታዊ ስራ) ላይ ማትኮር፣ | ➢ ሥራን በዕቅድ በመምራት፣<br>➢ ለስትራቴጂካዊ ጉዳዮችን ትኩረት ሰጥቶ በመስራት፣ |
| የክትትልና ግምገማ አሠራር በጥራትና በውጤት ላይ ያተኮረ አለመሆንና ሥራን መሠረት ያደረገ የግምገማ ባህል ያለመዳበር፣ | ➢ አፈፃፀምን ከውጤትና ከጥራት አንፃር በመገምገም፣<br>➢ የግምገማ ውጤትን መሠረት በማድረግ ቀጣይ የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ፣<br>➢ መልካም ተሞክሮዎችና ልምዶችን መቀመርና በማስፋት፣<br>➢ ግምገማን ወቅቱን የጠበቀ፣ሥርዓት ያለው እና በመርህ የተመሠረተ እንዲሆን በማድረግ፣<br>➢ አመራሩ የክትትል እና ድጋፍ ስርዓቱን በማጠናከር እንዲተገብር ማድረግ፣ |
| የአገልግሎት አሰጣጥ መሻሻል የሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ፣ | ➢ መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናቱን መሠረት ያደረገ አገልግሎት በመስጠት፣<br>➢ አገልግሎት አሰጣጡን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን በማድረግ፣<br>➢ በፈፃሚው ዘንድ የአገልጋይነትና የባለቤትነት ስሜት በማጎልበት፣<br>➢ ቅሬታዎችን ተቀብሎ በመመርመር የመፍትሔ እርምጃዎችን በመውሰድ፣<br>➢ የአገልግሎት አሠጣጥ ደረጃን ለመለካት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት፣<br>➢ የሚነሱ ቅሬታዎችንና አቤቱታዎችን አሰባስቦ በመተንተን ዘላቂ መፍትሔዎችን በመውሰድ፣<br>➢ የመልካም አስተዳደር እቅድንና የዜጎች ቻርተርን በሥራ ላይ በማዋል፣<br>➢ የተቋሙንና የሠራተኛውን የአፈጻፀም ምዘና በማድረግ የማስተካከያ ርምጃዎችን በመውሰድ፣ |
| የሥራ አመራር ብቃት በሚፈለገው ደረጃ አለመድረስ፣ | ➢ በየደረጃው ያሉ አመራሮችን በስልጠናና በትምህርት በማብቃት፣<br>➢ በየደረጃው በሚገኙት አመራሮች መካከል የልምድ ልውውጥ በማድረግ፣<br>➢ እውቀትን በማስተላለፍ ተተኪ አመራርን በየደረጃው በማብቃት፣ |
| ከመንግሥት በጀት ውጭ ሀብት የማፈላለግ ሥራ ውስንነቶች መኖራቸው፣ | ➢ ፕሮጀክት መቅረፅ የሚያስችል አቅም በመፍጠር፣<br>➢ ለተቋሙ ሥራ አጋዥ የሆኑ ፕሮጀክቶች በመቅረፅ ለጋሽ ድርጅቶችን በማፈላለግ፣<br>➢ በተገኙ የፕሮጀክት ድጋፎች አፈፃፀም ላይ ጠንካራ ክትትልና ግምገማ በማድረግ፣<br>➢ በመርህ ላይ የተመሠረተ ጠንካራ ግንኙነት ከለጋሽ ድርጅቶች ጋር በመፍጠር፣ |
| የመረጃ አያያዝ ሥርዓትና ባህል አለማዳበር፣ | ➢ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ የመረጃ አያያዝ ሥርዓት በመዘርጋት ጥቅም ላይ በማዋል፣<br>➢ በሙያው የተካኑና በቂ ባለሙያዎች በተቋሙ እንዲኖሩ በማድረግ፣<br>➢ የስታትስቲክስ መረጃዎችን በተጠናከረ መልክ በመያዝ፣ |
| የመሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ የተጠኑ ጥናቶች በተሟላ ሁኔታ አለመተግበር፣ የተከለሱ የጥናት ሰነዶችን አጸድቆ አለመተግበር፣ መጠናት የሚገባቸውን ስራ ክፍሎች አለማጥናት፣ | ➢ የተጠኑ መሰረታዊ የስራ ሂደቶች ጥናቶችን በአግባቡ መተግበር፣<br>➢ የተከለሱ የጥናት ሰነዶችን አጸድቆ መተግበር፣<br>➢ መጠናት የሚገባቸውን የስራ ክፍሎት ማጥናትና አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን ማሟላት፣ |
| ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ አደንዛዥ ዕፅና አልኮል ተጠቃሚነት እየተስፋፋ መምጣት፣ እንዲሁም በሴቶችና ህጻናት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፣ ሽብርተኝነት፣ የህይማኖት አክራሪነትና ሌሎች የወንጀል ፍትሕ ሥርዓቱን ውጤታማነት የሚፈታተኑ ወንጀሎች መኖራቸው፣ | ➢ ወንጀሎቹ እንዳይፈፀሙ ከፍትሕ አካላት፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ሌሎች አካላትና ከህብረተሰቡ ጋር በቅንጅትና በትብብር በመሥራት፣<br>➢ በወንጀሎቹ ዙሪያ ተከታታይነት ያላቸው ሥልጠናዎችንና ትምህርቶችን ለህብረተሰቡና ለባለሙያዎች በመስጠት ግንዛቤ በመፍጠር፣<br>➢ ወንጀሎቹ የሚያስከትሉትን ማህበራዊ ቀውስ አስመልክቶ ጥናቶችን በማድረግ የመፍትሄ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ፣<br>➢ በወንጀሎቹ ላይ ትኩረት ሰጥቶ በመስራት፣<br>➢ የባለሙያዎችን አቅም በመገንባት፣ |
| ከነባራዊው ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ እና ነባራዊ ሁኔታውን የሚሸፍኑ የሕግ ማዕቀፎች አለመኖራቸው፣ | ➢ በየጊዜው የሚፈጠሩና የሚነሱ አዳዲስ ሁኔታዎችን በመለየት የተሟላ የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖራቸው በማድረግ፤<br>➢ ከክልሉ የኢኮኖሚ ዕደገት ጋር የሚጣጣም የሕግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ፣ |
| የወንጀል ፍትህ ፖሊሲውን ለመተግበር የሚያስችሉ የአሰራርና የአደረጃጀት ሥርዓቶች አለመጠናከር፣ | ➢ በፖሊሲው ለተቋሙ የተሰጡ ተግባርና ኃላፊነቶችን መሠረት በማድረግ የአሰራርና የአደረጃጀት ሥርዓት በማጠናከር፣<br>➢ የሚወጡ ህጎች ከፖሊሲው ጋር እንዲጣጣሙ በማድረግ፣ |
| ለድጋፍ ሰጭው ሰራተኛ የአቅም ግንባታና የደመወዝና ጥቅማጥቅም ዙሪያ ውስንነቶች መኖራቸው | ➢ ዕቅድን መሰረት ያደረገ ተከታታይነት ያለው የስራ ላይ ስልጠና መስጠት፣<br>➢ ዮክልሉን ዓቅም ባገናዘበ መልኩ በተጠናው ጥናት መሰረት መተግበር፣ |

| ፈታኝ ሁኔታዎች | የመፍትሔ እርምጃዎች |
|---|---|
| ቅንጅታዊ አሰራር በሚፈልገው ደረጃ በቁርጠኝነት አለመምራት፣ | ➢ ክፍተቶችን በመለየት የፍትህ ስርዓቱ ውጤታማ በሚሆንበት መንገድ እንዲመራ ማስቻል፣ |
| የግዥ ስርዓቱ ለብክነት ና ለኪራይ ሰብሳቢነት ተጋላጭ መሆኑ፣ | ➢ የውስጥ ኦዲትን ፣ የመንግስት የግዥ ስርዓትን እና ተጠያቂነትን በማጠናከር፣ |
| ስራዎችን ከተቋሙ እሴቶች ጋር አስተሳስሮ የመስራት ባህል አለመዳበር፣ | ➢ በተቋሙ ዕሴቶች ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ማሰረጽ፣ |
| የተፈጠረውን የፖለቲካ ምህዳር ያለአግባብ መጠቀም | ➢ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስርዓት መዘርጋት እና ህጋዊ እርምጃ መውሰድ፣ |
| የለውጥና መልካም አስተዳደር ስራዎች በተሟላ ሁኔታ ስራ ላይ ያለመዋል፣ | ➢ የግንዛቤ ማሳደግ ስራዎችን አጠናክሮ መቀጠል፣<br>➢ የክትልና ግምገማ እንዲሁም የተጠያቂነት ስርዓቱን ማጠናከር፣ |
| ስራዎች በወቅቱና በጥራት ያለመከናወን፣<br>የአገልግሎት አሰጣጡ ክፍተት ያለበት መሆን | ➢ የለውጥ ስራዎችን በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ማድረግ፣<br>➢ የክትልና ግምገማ እንዲሁም የተጠያቂነት ስርአቱን ማጠናከር፣ |
| የዋጋ ግሽበት በበጀት አጠቃቀም ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ | ➢ ከመንግስት በጀት ውጪ ሌሎች ምንጮችን አፈላልጎ መጠቀም፣<br>➢ ለተቋሙ የተፈቀደውን በጀት በቁጠባ መጠቀም፣ |
| ብቃት ያለው የሰው ሀይል በበቂ ቁጥር ያለመኖር | ➢ ተመጣጣኝ የክፍያና ማበረታቻ ሥርዓት ስራ ላይ በማዋል ሰራተኛ ማሟላት፣<br>➢ በስራ ላይ ያለውን ሰራተኛ ማብቃት፣ |
| ለስራ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች አለመሟላት፣ | ➢ ጠንካራ የመረጃ ማዕከል ማቋቋም ፣<br>➢ ከተለያዩ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመመስረት መረጃ ለማግኘት ጥረት ማድረግ፣ |
| ከባለድርሻ አካላት ጋር በበቂ ሁኔታ ተቀናጅቶ ያለመስራት፣ | ➢ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመመስረት ቢጋራ መስራት፣ |
| የዕቅድ ዝግጅት፣ክትትልና ግምገማ ስርዓቱ ጠንካራ ያለመሆን | ➢ የዕቅድዝግጅት፣ክትትልና ግምገማ ክህሎትን ማሳደግ፣<br>➢ የተጠያቂነት ስርዓቱን ማጠናከር፣ |
| ሰራዎችን ከተቋሙ እሴቶች ጋር አስተሳስሮ የመስራት ባህል አለመዳበር፣ | ➢ በተቋሙ ዕሴቶች ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ማሰረጽ፣ |
| የስራ ተነሳሽነት ያለመጠናከር | ➢ የማበረታቻ ሥርዓት ሥራ ላይ ማዋል<br>➢ የተጠያቂነት ስርዓቱን ማጠናከር፣ |

# ክፍል ሶስት

## የሰባት ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ (ከ2016 እስከ 2022 ዓ/ም)

## 3.1. የዕቅዱ መነሻ፣ ዓላማ፣ አስፈላጊነት እና ወሰን

### 3.1.1. የዕቅዱ መነሻ

- የተቋማቱ ያለፈው 3 ዓመት (ከ2013 እስከ 2015 ዓ/ም) የልማት ዕቅድ አፈጻጸም፣
- ተቋማቱ በነባሩ ክልል 2 የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመናት ያላቸው ጥንካሬና ድክመት፤
- የተቋማቱ ማቋቋሚያ አዋጅ፤
- የኢ/ፌ/ድ/ሪ ፍትህ ሚኒስቴር የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ፤
- የነባሩ ክልል (የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክልል) የ10 ዓመት ስትራቴጂክ ዕቅድ፤
- የኢ/ፌ/ዴ/ሪ የወንጀል ፍትህ ፖሊሲ፤
- የፌደራልና የክልሉ ሕገመንግስት፣ አግባብነት ያላቸው ሕጎችን፣ የመንግሥት የልማት ዕቅዶችን እና አቅጣጫዎች በመቃኘት፤
- የሰብአዊ መብቶች አጠባበቅ የድርጊት መርሃ ግብር፤
- ብሔራዊ የፍልሰት መከላከል 5 ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ፤
- አገር አቀፍ የተቀናጀ የወንጀል መከላከል ስትራቴጂ፣
- የተቋማቱ የተገልጋይ እርካታ ዳሰሳ ጥናት ውጤቶችን በመገምገም፤
- የለውጥ መሳሪያዎች ሰነዶች እና የመልካም አስተዳደር ንቅናቄ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት፣

### 3.1.2. የዕቅዱ ዋና ዋና ዓላማ

- የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ የሕብረተሰቡን ሠላምና ደህንነት ማረጋገጥ፣
- በፍትሐብሔራዊ ጉዳይ የመንግስትና የህዝብን ጥቅም ማስጠበቅ፣
- ጥራት ያላቸው የህግ ማዕቀፎች ማዘጋጀት፣ የንቃተ ህግ ግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በስፋት በመስራት መብትና ግዴታውን ያሚያውቅ ማህበረሰብ መፍጠር፣
- የዜጎች ሰብዓዊ መብት በማስከበር ዋስትና ያለው ዲሞክራሲ መገንባት፣
- የህግ ታራሚዎች በአግባቡ የታረሙና የታነጹ በማድረግ አምራች ዜጋ እንዲሆኑ  ማድረግ፣
- ችግር ፈቺ የሆኑ የህግ ጥናትና ምርምር ስራዎች በመስራት አዲስ ለሚረቁና ለሚሻሻሉ ህጎች የግብአት ምንጭ ማድረግ፣
- የህግ ባለሙያዎች የአቅምና የክህሎት ክፍተቶችን በጥናት በመለየት የአቅም ግንባታ ስልጠና በመስጠት በሴክተሩ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ደረጃ በደረጃ በመቅረፍ ተቋማቱ ተልዕኳቸው በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡

### 3.1.3. የዕቅዱ ወሰን

ይህ ዕቅድ ተግባራዊ የሚሆነው በክልሉ ፍትህ ቢሮ፣ በተጠሪ ተቋማት እና በስር መዋቅር በሚገኙ ተቋማት ይሆናል፡፡

### 3.2. የትኩረት አቅጣጫዎች

የአመራሩና የባለሙያው የቅድመ ስራ፣ የስራ ላይና ሌሎች አጫጭር ስልጠናዎች በመስጠት የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ማሳደግ፣ የመንግስትና ህዝብን ጥቅም ማስከበር፤ የልማት፣ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር ግንባታን ማጠናከር፤ የህግ የበላይነትን ማስከበር፣ የዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ማረጋገጥ፣ የህግ ታራሚዎች የታረሙና የታነጹ ማድረግ፣ ችግር ፈቺ የህግ ጥናትና ምርምር ስራዎች በመስራት በተቋማቱ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ፍትሃዊ እና ግልጸኝነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ ትኩረት የሚሠጥባቸው ይሆናሉ፡፡

### 3.3. ማስፈፀሚያ ስልቶች

- የማስፈፀም አቅምን በመግንባት ተቋማዊ ለውጥ ለማምጣት የለውጥ መሳሪያዎችንና የአሰራር ስርዓቶችን በመተግበር፤
- የመልካም አስተዳደር መርሆችን በመከተል በወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ ሲቪል ማህበራት፣ ባለድርሻ አካላት እና የህዝብ ክንፍ በማሳተፍ የራሳቸውን ሚና እንዲወጡ በማድረግ፤
- በሙስና፣ በታክስ እና በከባድ ወንጀሎች ምርመራ ከፖሊስ ጋር አብሮ በመስራት ቅንጅታዊ አሰራርን በማጎልበት፤
- ከባለድርሻ አካላት ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከር አገልግሎት አሰጣጡ ቀልጣፋና ውጤታማ ማድረግ፤
- የህዝብና የመንግስት ጥቅም ያለባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ከሴክተር መ/ቤቶች በቅንጅት በመስራት፤
- የህብረተሰቡን የንቃተ ሕግ ደረጃ በማሻሻል ሕግና ሥርዓት የሚያከብርና የህግ ማስከበር ስራውን በንቃት የሚደግፍ አደረጃጀት በመፍጠር ሕጎች ለህብረተሰቡ በልዩ ልዩ መንገድ እንዲታወቁና እንዲሠራጩ በማድረግ፤
- ጠበቆች ለፍትህ ሥርዓቱ አጋዥ የሚሆኑበትን ስርዓት በመዘርጋት፤
- ልዩ ትኩረት የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ጥቅሞች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ነፃ የሕግ ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ፣
- በታራሚዎች የተሃድሶ ልማት ከባለድርሻ እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት፣
- የክፍተት ዳሰሳ ጥናት በማድረግ የረጅም፣ የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ስልጠና በመስጠት የባለሙያዎች የመፈጸም አቅም በመገንባት፣
- የተቋሙን መሪ የልማት ዕቅድ ወደ ፈጻሚ አካላት በማውረድ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ግብረ-መልስ በመስጠት፤
- ወጥነትና ተከታታይነት ያለው የክትትል፣ ድጋፍ እና የአፈጻጸም ግምገማ ስርዓት በመዘርጋትና የመረጃ ፍሰትና ግብረ-መልስ አሰጣጥ ስርዓትን የተቀላጠፈ በማድረግ፣
- ለተቋማቱ ተገቢውን የሰው ኃይል እንዲሟላ በማድረግ፤
- ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የመረጃ አያያዝ ስርዓቱን እንዲሻሻል በማድረግ፣

### 3.4. የ7 ዓመታት ስትራቴጂክ ዕቅድ ዋና ዋና ግቦችና ተኮር ተግባራት

**ግብ 1፡- የወንጀል ጉዳዮች አስተዳደር ጥራት እና ውጤታማነት ማሳደግ**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- ከፖሊስ ጋር በጋራ ሊጣሩ በሚገቡ የወንጀል ምርመራ ምጣኔ በ2015 ካለበት 95% ወደ 100% ማሳደግ፤

- የመዝገብ የማጥራት ምጣኔን በ2015 ዓ/ም ካለበት 93.8% ወደ 99% ማሳደግ፣
- የመዝገብ የመንጠባጠብ ምጣኔን በ2015 ዓ/ም ካለበት 5.9% ወደ 3% መቀነስ፣
- በመዝገብ የማስቀጣት ምጣኔን በ2015 ዓ/ም ካለበት 95.7% ወደ 99% ማድረስ፣
- በተከሳሽ የማስቀጣት ምጣኔን 95% ማድረስ፤
- በዕርቅ ማለቅ የሚገባቸው ቀላል የወንጀል መዝገቦች ከ33% ወደ 75% ማድረስ፣
- በጠቋሚዎችና በምስክሮች የሚቀርቡ የከለላ ጥያቄዎች ምላሽ የመስጠት ምጣኔን ወደ 100% ማሳደግ፣
- ዐ/ህግ ይግባኝ በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ ምጣኔ በመዝገብ **ከ73.7% ወደ 90%** ማድረስ፣
- ዐ/ህግ ይግባኝ በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በተከሳሽ 95% ማድረስ፣
- ተከሳሾች ይግባኝ የጠየቁባቸው ጉዳዮች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም በመዝገብ ከ88.2% ወደ 95% ማድረስ፣
- ተከሳሾች ይግባኝ የጠየቁባቸው ጉዳዮች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም በተከሳሽ 95% ማድረስ፣
- ዐ/ህግ ሰበር በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በመዝገብ ከ67% ወደ 90%
- ዐ/ህግ ሰበር በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በተከሳሽ 95% ማድረስ፣
- ተከሳሾች ሰበር የጠየቁባቸው ጉዳዮች በመዝገብ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም ከ88.8% ወደ 95% ማድረስ፣
- ተከሳሾች ሰበር የጠየቁባቸው ጉዳዮች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም በተከሳሽ 95% ማድረስ፣
- በሴቶችና ህጻናት አረጋውያንና በአካል ጉደተኞች የመዝገብ የማጥራት ምጣኔን ከ96% ወደ 100% ማድረስ፣
- በሴቶችና ህጻናት አረጋውያንና በአካል ጉደተኞች የመዝገብ የመንጠባጠብ ምጣኔን በ2015 ዓ/ም ካለበት 5% ወደ 2% መቀነስ፤
- በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የማስቀጣት ምጣኔንን በመዝገብ ከ91.6% ወደ 99% ማድረስ፣
- በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች የማስቀጣት ምጣኔን በተከሳሽ 97% ማድረስ፣
- በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ዐ/ህግ ይግባኝ በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በመዝገብ ከ89.7% ወደ 96% ማድረስ፣

- በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ዐ/ህግ ይግባኝ በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በተከሳሽ 97% ማድረስ፣
- በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ተከሳሾች ይግባኝ የጠየቁባቸው ጉዳዮች በመዝገብ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም ከ83% ወደ 96% ማድረስ፣
- በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ተከሳሾች ይግባኝ የጠየቁባቸው ጉዳዮች በተከሳሽ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም 97% ማድረስ፣
- በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ዐ/ህግ ሰበር በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በመዝገብ ከ86% ወደ 96% ማድረስ፣
- በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ዐ/ህግ ሰበር በጠየቁባቸው መዝገቦች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን እንዲሻር ወይም እንዲሻሻል የማድረግ አቅምን በተከሳሽ 97% ማድረስ፣
- በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ተከሳሾች ሰበር የጠየቁባቸው ጉዳዮች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም በመዝገብ ከ87% ወደ 96% ማድረስ፣
- በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን በተመለከተ ተከሳሾች ሰበር የጠየቁባቸው ጉዳዮች የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ አቅም በተከሳሽ 97% ማድረስ፣
- በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች የፍትሐብሔር የመርታት ምጣኔን 95% ወደ 99% ማድረስ፣
- በዕቅድ ዘመኑ በ4,025 የዐቃቤ ህግ መዝገቦች ላይ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ማድረግ፣
- ለሚቀርቡ ወንጀል ነክ አቤቱታዎችና ጥቆማዎች የመጀመሪያ ደረጃ ውሣኔ የመስጠት ምጣኔ 100% ማሳደግ፣

**ግብ 2፡- የመንግስትና የህዝብ የሚመለከቱ የፍትሐብሔር ጉዳዮች ውጤታማነት ማሳደግ**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- የመንግስት የግዥ ህግ የተከተለ መሆኑን በማረጋገጥ 100% በወቅቱ ማጽደቅ፣
- መንግስት ከሳሽ በሆነበት ፍትሐብሔር ጉዳዮች የመርታት ምጣኔን 90% ወደ 96% ማድረስ፣
- መንግስት ተከሳሽ በሆነበት የፍትሐብሔር ጉዳዮች የመርታት ምጣኔ 90.6% ወደ 96% ማድረስ፣
- ለመንግስት ተቋማት በፍትሀብሄር ጉዳዮች 100% የህግ ምክር ማሳደግ፣
- በፍ/ቤት ውሳኔ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የተወሰነ ገንዘብ/ሀብት ካለበት 68.1% ወደ 90% ማስመለስ፣
- የፍትሐብሔር ጉዳይ ከክስ በፊት በድርድር ሀብት እንዲመለስ የማድረግ አቅም 14.9% ወደ 30% ማሳደግ፣
- በሙስና የተመዘበረ የመንግስት ሀብትና ንብረት የማስመለስ ምጣኔ ካለበት 73.3% ወደ 90% ማሳደግ፣
- በታክስ ማጭበርበር የተመዘበረ የመንግስት ሀብትና ንብረት የማስመለስ ምጣኔ ከ75.2% ወደ 95% ማሳደግ፣

- ዐቃቤ ህግ ይግባኝ የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የማሻር/የማሻሻል/ ምጣኔ ከ89.3% ወደ 99% ማሳደግ፣
- ተከሳሾች ይግባኝ የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር መዝገቦች ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ ምጣኔ ከ87.3% ወደ 95% ማሳደግ፣
- ዐቃቤ ህግ ሰበር የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ የማሻር/የማሻሻል/ 99% ማድረስ፤
- ተከሳሽ ሰበር የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳዮች የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና የማድረግ ምጣኔ 95% ማድረስ፣

**ግብ 3፡- የሰብአዊ መብት አያያዝና ጥበቃ ውጤታማነት ማሳደግ፣**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሃ-ግብር ፈጻሚ ሴክተር መ/ቤቶች ሰብዓዊ መብትን በዕቅዳቸው ሜንስትም እንዲያደርጉ መከታተል፤
- በሰብዓዊ መብት የድርጊት መርሃ ግብሩ መሰረት ከፈጻሚ አካላት የዕቅድ አፈጻጸም ወቅቱን ጠብቀው እንዲልኩ በየሩብ ዓመቱ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣
- የፈጻሚ ተቋማት የሰብዓዊ ድርጊት መርሀ ግብር መነሻነት የሚያቀርቧቸውን ዕቅድ አፈጻጸም በየግማሽ ዓመቱ መገምገምና ግብረ-መልስ መስጠት፣
- በሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ዙሪያ ለፈጻሚ ተቋማት አመራሮችና ፈጻሚዎች 7 የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረክ ማዘጋጀት፣
- በሰብዓዊ መብት ህግጋት ዙሪያ የተለያዩ የሲቪክ ማህበራትን እና ተቋማትን በማስተባበር 7 የግንዛቤ መፍጠር መድረክ ማዘጋጀት፣
- የተጠርጣሪዎች ማቆያ/ማረፊያ/ ቤት በሳምንት 2 ጊዜ ጉብኝት በማድረግ ሰብዓዊ መብታቸውን ማስከበር፤
- ማረሚያ ቤቶች በወር 1 ጊዜ ጉብኝት በማድረግ የታራሚዎች ሰብዓዊ መብታቸውን ማስከበር፤
- የሰብዓዊ መብት ጥሰት በፈፀሙ አካላት ላይ 100% በህግ እንዲጠየቁ ማድረግ፤

**ግብ 4፡- የህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና ቁጥጥር ውጤታማነትን ማሳደግ**

**ዝዋና ዋና ተግባራት**

- የፀረ-ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ግብረ-ኃይል በየግማሽ ዓመቱ የዕቅድና ሪፖርት ግምገማ ማድረግና ግብረ-መልስ መስጠት፣
- ለታችኛው መዋቅር የፀረ-ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ግብረ-ኃይል በየግማሽ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
- በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ቁጥጥርና መከላከል ዙሪያ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ 14 መድረክ ማዘጋጀት፣
- የህገ ወጥ ሰዎች ዝውውር ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የተጋላጭነት ሁኔታ ከቦታ፣ ከተጎጂዎችና ከአዘዋዋሪዎች አንጻር ጥናት ማካሔድ፣

**ግብ 5፡- የይቅርታ አሰጣጥ ስራን ጥራትና ውጤታማነት ማሳደግ**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- የይቅርታ ህጉን የሚያሟሉ የህግ ታራሚዎች 100% የይቅርታ ተጠቃሚ ማድረግ፣
- ለህግ ታራሚዎች የሚሰጠው የይቅርታ ምልመላና የውሳኔ አስተያየት ጥራት 100% ማረጋገጥ፤
- ከህጻን ጋር ያሉ እናቶች፣ አረጋውያንና የማይድን በሽታ ታማሚ የሆኑ የህግ ታራሚዎች 100% በልዩ ሁኔታ የይቅርታ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- የአመክሮ ጊዜያቸው የደረሰ የህግ ታራሚዎች ለፍ/ቤት ጥያቄ በማቅረብ እንዲፈቱ ማድረግ፤
- በዕቅድ ዘመኑ በይቅርታ አሰጣጥ ፋይዳ ዙሪያ 2 የዳሰሳ ጥናት ማድረግ፤

**ግብ 6፡- የህግ ጥናትና ማርቀቅ ስራን ጥራትና ውጤታማነትን ማሳደግ፣**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በዕቅድ ዘመኑ እንዲረቀቁና አስተያየት እንዲሰጥባቸው የሚቀርቡ ሕጎች 100% የህግ ማርቀቅና ቅርጽ የማስያዝ ስራን መስራት፣
- ወደ እንግሊዘኛ እንዲተረጎም የሚቀርቦች ህጎች 100% የትርጉም ስራ መስራት፤
- በስራ ላይ በሚገኙ ህጎች ላይ 7 የፋይዳ ጥናት ማድረግ፤
- ለክልሉ መንግስት፣ ለሴክተር መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች **የህግ ጉዳይ ጥያቄ** 100% ምላሽ መስጠት፤

**ግብ 7፡- የህብረተሰቡን ንቃተ ህግ ማሳደግ**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በየበጀት ዓመቱ ለሚሰጠው የንቃተ ህግ ትምህርት 7 የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማድረግ፣
- ለተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጡ የንቃተ ህግ ግንዛቤ መስጫ 350 ማንዋሎችን ማዘጋጀት፣
- በሬድዮና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ የንቃተ ሕግ ትምህርት ማስተማሪያ በየበጀት ዓመቱ 52 ፕሮግራም ማዘጋጀት፤
- የተለያዩ የማስተማሪ መድረኮች፣ የሴቶች የልማት ቡድን እና ሌሎች አደረጃጀቶችን በመጠቀም በፊት ለፊት መድረክ የንቃተ ህግ ትምህርት የተሰጣቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች 2015 ካለበት 415,572 ወደ 560,000 ማሳደግ፤
- በኤሌክትሮኒክ እና በሕትመት ሚዲያ የንቃተ ህግ ትምህርት ያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በቁጥር ካለበት 2,454,312 ወደ 3,000,000 ማሳደግ፤
- በማረሚያ ተቋማት የሚገኙ ታራሚዎች በተለያዩ የሕግ ርዕሰ ጉዳዮች የንቃተ ሕግ ትምህርት የመስጠት አቅም አሁን ካለበት 2,758 ወደ 7,390 ማሳደግ፤
- ከክልሉ ዩኒቨርሲቲዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት በየበጀት ዓመቱ 3 የስልጠና መድረኮች በማዘጋጀት በተለያዩ የህግ ጉዳዮች ላይ ለባለሙያዎች ስልጠና መስጠት፤
- እስከ ዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 30,500 ኮፒ የንቃተ ሕግ ማስተማሪያ ቡክሌትና ብሮሸር በማሳተም ማሰራጨት፤
- የተሰጡ የንቃተ ህግ ትምህርቶች ተደራሽነትና ያስገኙትን ፋይዳ 7 ጥናት ማድረግና የማሻሻያ እርምጃ መውሰድ፣

**ግብ 8፡- የህጎች ተደራሽነትን ማሳደግ፣**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2022 ዓ.ም የወጡ የክልል ህጎችን ማሰባሰብና ማደራጀት፣

- ተሰብስበው የተደራጁ የፌደራልና የክልል ህጎችን በ2,000 ኮፒ ማሳተም፣
- የተሰበሰቡ ህጎች 100% ለህብረተሰቡና ለተቋማት ተደራሽ ማድረግ፣

**ግብ 9፡- ጠበቆች ለፍትህ ሥርዓቱ ኢጋዥነታቸውን ማጠናከር፣**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- ጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች የፍትህ ስርዓቱ ኢጋዥ ኃይል ለማድረግ ከሙያቸውና ከሥራቸው ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ 7 ሥልጠና መስጠት፣
- ለጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ፈቃድ የመስጠትና የማደስ አገልግሎት 100% ውጤታማነትን ማሳደግ፣
- ጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች በሚሰጡት የጥብቅና አገልግሎት ላይ በየግማሽ ዓመቱ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣
- በጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን 100% በዐቃቤ ህግ ውሳኔ መስጠት፣
- የሥነ-ምግባር ጉድለት በሚያሳዩ ጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ላይ የሚቀርቡ ክሶችን በድስፕሊን ጉባኤ 100% ውሳኔ ማሰጠት፣
- ክስ የተመሰረተባቸው ጠበቆችና የህግ ጉዳይ ፀሐፊዎች 98% ጥፋተኝነታቸው ማሰኘት፤
- ጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ለህብረተሰቡ በሚሰጡት አገልግሎትና ከፍትህ አካላት ጋር ባላቸው መስተጋብር ዙሪያ በግማሽ ዓመቱ የመወያያ መድረክ ማዘዘጋጀት፣
- ጠበቆችና ነጻ የህግ ድጋፍ ማዕከላት አቅም ለሌላቸው ዜጎች የሚሰጡትን ነጻ የጥብቅና አገልግሎት ውጤታማነት ማሳደግ፣
- ለጠበቃ የመክፈል አቅም ለሌላቸው ሴቶች፣ ህጻናት፣ አካል ጉዳተኞችና ለአረጋውያን ነጻ የጥብቅና አገልግሎት 100% እንዲያገኙ ማድረግ፣
- ክልላዊ የጠበቆች አስተዳደር አዋጅ ማዘጋጀት፤

**ግብ 10፡- ዜጎች በሲቪል ማህበራት የመደራጀት መብታቸውን ማረጋገጥ፣**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- ክልላዊ የሲቪል ማህበራት አዋጅ ማዘጋጀት፣
- የሲቪል ማህበራት የምዝገባና የዕድሳት አገልግሎት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ 100% ማከናወን፣
- የሲቪል ማህበራት ለተቋቋሙበት ዓላማ ስለመንቀሳቀሳቸው በየግማሽ ዓመቱ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣
- የሲቪል ማህበራት ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በጊዜ ገደቡ አጣርቶ 100% ምላሽ መስጠት፣

**ግብ 11፡- የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት ውጤታማነትን ማሳደግ፣**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- የሠነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎትን በህጉ መሰረት መከናወኑ በየሩብ ዓመቱ ኦዲት ማድረግ፣
- የሠነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር የሚዘጋ የአሰራር ስርዓት 100% ማጠናከር፤
- በሠነድ ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት ዙሪያ ለአመራሩና ለፈጻሚዎች ስልጠና መስጠት፤

**ግብ 12፡- ለታራሚዎች ተሀድሶ ልማት ግንባታ መስጠት**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ (2022 ዓ/ም) የህግ ታራሚዎች በቀለም ትምህርት የቅበላ መጠን አሁን ካለበት 2,182 ወደ 4,255 ማሳደግ፤
- በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የሚሰለጥኑ የህግ ታራሚዎች ቅበላ አሁን ካለበት 1,327 ወደ 6,352 ታራሚዎች ማሳደግ፤
- በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የምክክር አገልግሎት የሚያገኙ የህግ ታራሚዎች አሁን ካለበት 2,960 ወደ 9,221 ማሳደግ፤
- በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ የሥነ ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርት የሚወሰዱ የህግ ታራሚዎች አሁን ካለበት 3,207 ወደ 8,426 ማሳደግ፤
- እስከ በዕቅድ ዘመኑ መጨረሻ 840 ታራሚዎች የኮ-ካውንስለርነት ስልጠና ማሰልጠን፤
- ታራሚዎች በየሙያ ዘርፍ በማህበር በማደራጀት የገቢ መጠናቸው 100% ማማደግ፣
- 1 ዘመናዊ የግብርና እና የዕደ ጥበብ ማዕከላት ማስገንባት፤
- 1 የወጣት ጥፋተኞች የተሀድሶ ማዕከል ማቋቋም፤

**ግብ 13፡- የታራሚዎች መሰረታዊ ፍላጐት ማሟላት፣**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- የታራሚዎች ምግብ በሚኒማ መሠረት 100% ማቅረብ፤
- የታራሚዎች የመጠጥና የንጽህና መጠበቂያ ውሃ አቅርቦት 100% ማረጋጥ፤
- የታራሚዎች የጤና አገልግሎት ሽፋን 100% ማረጋጥ፤
- የህግ ታራሚዎች የመዝናኛ ክበባት 100% ማሟላት፤
- 1 የሥነ-አእምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል ማቋቋም፤
- 2 አዳዲስ የታራሚዎች መጠለያ መገንባት፤

**ግብ 14፡- የታራሚዎች ደህንነት ማረጋገጥ**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- የማረሚያ ተቋማት የጥበቃና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት 100% ማጠናከር፤
- ለታራሚዎች የተቋሙ ዓላማ፣ ደንብና መመሪያ 100% እንዲያውቁ ማስተማር፤
- ወደ ማረሚያ እንዳይገቡ የተከለከሉ ቁሳቁሶች ላይ የቁጥጥር ስርዓቱ 100% ማጠናከር
- በዕቅድ ዘመኑ 280 የማረሚያ ፖሊስ አባሎች የተሃድሶ ስልጠና መስጠት፤
- በዕቅድ ዘመኑ 700 አዲስ የማረሚያ ምልምል ፖሊሶች ማሰልጠን፤

**ግብ 15፡- የፍትህ አካላት የህግ ባለሙያዎች አቅም ማሳደግ**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በዕቅድ ዘመኑ ለ336 የህግ ባለሙያዎች የቅድመ ሥራ ስልጠና ማሰልጠን፤
- በዕቅድ ዘመኑ ለ364 የህግ ባለሙያዎች የሥራ ላይ ስልጠና ማሰልጠን፤
- በዕቅድ ዘመኑ ለ2,800 የህግ ባለሙያዎች አጫጭር ስልጠና ማሰልጠን፤
- በየበጀት ዓመቱ የስልጠና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማድረግ፤
- 2 ጊዜ የስልጠና ፋይዳ ጥናት ማካሄድ፤

**ግብ 16፡- በህጎች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ ውጤታማነታቸው ማረጋገጥ**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በየበጀት ዓመቱ የምርምር ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፤
- በተመረጡ 28 ህጎች ላይ ጥናትና ምርምር ማድረግ፤
- 2 ጊዜ በጥናትና ምርምር ውጤቶች ላይ የፋይዳ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ፤
- በክልሉ ከሚገኙ ዩኒቨርስቲዎች መካከል በሕግ ጥናትና ምርምር ዙሪያ በየበጀት ዓመቱ አንዱን በማሳተፍ በቅንጅት መስራት፤

**ግብ 17፡- የፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም ተፈጻሚነት ማረጋገጥ**

**ዋና ዋና ተግባራት**

- በፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም ዙሪያ ለፍትህ አካላት 100% የማማከር ስራ መስራት፤
- በየበጀት ዓመቱ ክልል አቀፍ የፍትህ ሳምንት ማክበር፤
- በፍትህ ዘርፉ የሚከናወኑ የማሻሻያ ፕሮግራሞች አፈጻጸም ዙሪያ በሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፤
- በየግማሽ ዓመቱ የፍትህ ተቋማት ጥምረት መድረክ ማዘጋጀት፤
- የፍትህ መረጃዎችን ለጥናትና ምርምር በሚያመች መልኩ የማሰባሰብ የመተንተንና የማደራጀት 100% መስራት፤
- የመሰረተ ማህበረሰብ የፍትህ አገልግሎት እና አማራጭ የሙግት መፍቻ ሥርዓት መዘርጋት፤

# 3.5. የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ ግቦች፣ የግብ አመልካቶችና ዒላማዎች

| ግብ | የግብ አመልካች/መለኪያ | መስፈሪያ | መነሻ<br>የ2015 በት ዓመት አፈጻጸም | በዕቅድ ዘመኑ የሚደረስባቸው ዒላማዎች | | | | | | | ፈጻሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| የወንጀል ጉዳዮች አስተዳደር ጥራት እና ውጤታማነትን ማሳደግ፣ | ከፖሊስ ጋር በጋራ የተጣራ የወንጀል ምርመራ ምጣኔ፣ | በመቶኛ | 95% | 96% | 97% | 98% | 99% | 100% | 100% | 100% | |
| | 99% የደረሰ የመዝገብ የማጥራት ምጣኔ፣ | በመቶኛ | 93.8% | 95% | 95.5% | 96% | 96.5% | 97% | 98% | 99% | |
| | ወደ 2% የቀነሰ የመዝገብ መቋረጥ ምጣኔ | በመቶኛ | 5.9% | 5.75% | 5.5% | 5% | 4.5% | 4% | 3.5% | 3% | |
| | 99% የደረሰ በመዝገብ የማስቀጣት ምጣኔ | በመቶኛ | 95.7% | 95.75% | 96% | 96.25% | 96.5% | 97% | 98% | 99% | |
| | 95% የደረሰ በተከሳሽ የማስቀጣት ምጣኔ | በመቶኛ | --- | 91% | 91.5% | 92% | 92.5% | 93% | 94% | 95% | |
| | 65% በዕርቅ ያለቁ ቀላል የወንጀል ጉዳዮች | በመቶኛ | 33% | 35% | 40% | 45% | 50% | 65% | 70% | 75% | |
| | 100% የተሰጠ ለጠቋሚዎችና ምስክሮች ከለላ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | በመዝገብ 90% የደረሰ የዐ/ህግ ይግባኝ መዝገቦች እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | 73.7% | 75% | 78% | 81% | 84% | 86% | 88% | 90% | |
| | በተከሳሽ 95% የደረሰ የዐ/ህግ ይግባኝ መዝገቦች እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | --- | 80% | 82% | 84% | 87% | 89% | 92% | 95% | |
| | በመዝገብ ላይ 95% የደረሰ የተከሳሽ ይግባኝ መዝገቦች እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | 88.2% | 90% | 91% | 92% | 93% | 94% | 95% | 95% | |
| | በተከሳሽ ላይ 95% የደረሰ የተከሳሽ ይግባኝ መዝገቦች እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | --- | 90% | 91% | 92% | 93% | 94% | 95% | 95% | |
| | በመዝገብ 90% የደረሰ የዐ/ህግ ሰበር መዝገቦች እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | 67% | 70% | 75% | 80% | 83% | 85% | 88% | 90% | ፍትህ ቢሮ |
| | በተከሳሽ 95% የደረሰ የዐ/ህግ ሰበር መዝገቦች እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | --- | 80% | 82% | 84% | 87% | 89% | 92% | 95% | |
| | በመዝገብ 95% የደረሰ የተከሳሽ ሰበር እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | 88.8% | 89% | 90% | 91% | 92% | 93% | 94% | 95% | |
| | በተከሳሽ 95% የደረሰ የተከሳሽ ሰበር እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | --- | 90% | 91% | 92% | 93% | 94% | 95% | 95% | |
| | 100% የደረሰ በሴቶች፣ ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች የመዝገብ የማጥራት ምጣኔ | በመቶኛ | 96% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | ወደ 2% የቀነሰ በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች የመዝገብ የመቋረጥ ምጣኔ | በመቶኛ | 5% | 4.75% | 4.5% | 4% | 3.5% | 3% | 2.5% | 2% | |
| | በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመዝገብ 99% የደረሰ የማስቀጣት ምጣኔ | በመቶኛ | 91.6% | 97 | 97.25 | 97.5% | 97.75 | 98 | 98.5 | 99 | |
| | በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በተከሳሽ 97% የደረሰ የማስቀጣት ምጣኔ | በመቶኛ | -- | 92% | 93% | 94% | 95% | 96% | 97% | 97% | |
| | በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ | በመቶኛ | 89.7% | 90% | 91% | 92% | 93% | 94% | 95% | 96% | |

| ግብ | የግብ አመልካች/መለኪያ | መስፈሪያ | መነሻ የ2015 በት ዓመት አፈጻጸም | በዕቅድ ዘመኑ የሚደረስባቸው ዒላማዎች | | | | | | | ፈጻሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| | ወንጀሎች በመዝገብ 96% የደረሰ የዐ/ህግ ይግባኝ እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | | | | | | | | | | |
| | በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በተከሳሽ ላይ 97% የደረሰ የዐ/ህግ ይግባኝ እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | --- | 92% | 93% | 94% | 95% | 96% | 97% | 97% | |
| | በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመዝገብ ላይ 96% የደረሰ የተከሳሽ ይግባኝ እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | 83% | 90% | 91% | 92% | 93% | 94% | 95% | 96% | |
| | በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በተከሳሽ ላይ 97% የደረሰ የተከሳሽ ይግባኝ እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | --- | 92% | 93% | 94% | 95% | 96% | 97% | 97% | |
| | በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመዝገብ 96% የደረሰ የዐ/ህግ ሰበር እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | 86% | 90% | 91% | 92% | 93% | 94% | 95% | 96% | |
| | በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በተከሳሽ ላይ 97% የደረሰ የዐ/ህግ ሰበር እንዲሻሩ ወይም እንዲሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | --- | 92% | 93% | 94% | 95% | 96% | 97% | 97% | |
| | በሴቶችና ህጻናት አረጋውያን እና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በመዝገብ ላይ 96% የደረሰ የተከሳሽ ሰበር እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | 87% | 90% | 91% | 92% | 93% | 94% | 95% | 96% | |
| | በሴቶች፣ ህጻናት አረጋውያንና በአካል ጉደተኞች ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በተከሳሽ ላይ 97% የደረሰ የተከሳሽ ሰበር እንዲፀኑ ወይም እንዳይሻሻሉ የማድረግ ምጣኔ | በመቶኛ | --- | 92% | 93% | 94% | 95% | 96% | 97% | 97% | |
| | በሴቶችና ህጻናት፣ አረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች የፍትሐብሔር ጉዳዮች 99% የመርታት ምጣኔ | በመቶኛ | 95% | 96.5% | 97% | 97.5% | 98% | 98.5% | 99% | 99% | |
| | የህግ ኦዲትና ኢንስፔክሽን የተደረገባቸው 4,025 የዐቃቤ ህግ መዝገቦች | በቁጥር | 463 | 500 | 525 | 550 | 575 | 600 | 625 | 650 | |
| | ለሚቀርቡ ወንጀል ነክ አቤቱታዎችና ጥቆማዎች የመጀመሪያ ደረጃ ውሣኔ የመስጠት ምጣኔ 100% ማሳደግ፣ | በመቶኛ | 98% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| **የይቅርታና የአመክሮ አሰጣጥ ስራን ጥራትና ውጤታማነት ማሳደግ** | የይቅርታ ህጉን የሚያሟሉ የህግ ታራሚዎች በዓመት 2 ጊዜ የይቅርታ ተጠቃሚ ማድረግ፣ | በቁጥር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | ፍትህ ቢሮና ማረሚያ ኮሚሽን |
| | ለህግ ታራሚዎች የሚሰጠው የይቅርታ ምልመላና የውሳኔ አስተያየት ጥራት 100% ማረጋገጥ፤ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | በልዩ ሁኔታ የይቅርታ ተጠቃሚ የሆኑ የህግ ታራሚዎች ምጣኔ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | የታራሚዎች የአመክሮ ጥያቄ ማቅረብና ክትትል በመቶኛ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | ማረሚያ ኮሚሽን |
| | በይቅርታ አሰጣጥ ፋይዳ ላይ የተደረገ የዳሰሳ ጥናት በቁጥር | በቁጥር | | | | 1 | | | | 1 | ፍትህ ቢሮና ማረሚያ ኮሚሽን |
| **የመንግስትና የህዝብ የሚመለከቱ የፍትሐብሔር ጉዳዮች** | የመንግስት የግዥ ህግ የተከተለ መሆኑን በማረጋገጥ 100% በወቅቱ ማጽደቅ፣ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | **ፍትህ ቢሮ** |
| | 96% የደረሰ መንግስት **ከሳሽ** በሆነበት ፍትሐብሔር ጉዳዮች | በመቶኛ | 90% | 91.5% | 92% | 92.5% | 93% | 94% | 95% | 96% | |

| ግብ | የግብ አመልካች/መለኪያ | መስፈሪያ | መነሻ የ2015 በት ዓመት አፈጻጸም | በዕቅድ ዘመኑ የሚደረስባቸው ዒላማዎች | | | | | | | ፈጻሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| **ውጤታማነት ማሳደግ** | የመርታት ምጣኔ | | | | | | | | | | |
| | 96% የደረሰ መንግስት **ተከሳሽ** በሆነበት የፍትሐብሔር ጉዳይ የመርታት ምጣኔ | በመቶኛ | 90.6% | 91.5% | 92% | 92.5% | 93% | 94% | 95% | 96% | |
| | በፍትሀብሄር ጉዳዮች የተሰጠ የህግ ምክር ሽፋን ምጣኔ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | በፍትሀብሄር አፈጻጸም ክስ 90% ገቢ የተደረገ የመንግስት ሀብት | በመቶኛ | 68.1% | 75% | 80% | 83% | 85% | 87% | 89% | 90% | |
| | ከተመዘበረው ሀብት ላይ ከክስ በፊት በድርድር 30% ማስመለስ | በመቶኛ | 14.9% | 18% | 20% | 22% | 24% | 26% | 28% | 30% | |
| | ወደ 90% ያደገ በሙስና የተመዘበረ የመንግስት ሀብትና ንብረት የማስመለስ ምጣኔ | በመቶኛ | 73.3% | 78% | 80% | 82% | 84% | 86% | 88% | 90% | |
| | ወደ 95% ያደገ በታክስ ማጭበርበር የተመዘበረ የመንግስት ሀብት የማስመለስ ምጣኔ | በመቶኛ | 75.2% | 86% | 87% | 89% | 91% | 92% | 9% | 95% | |
| | 95% የደረሰ ተከሳሾች ይግባኝ የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳይ መዝገቦች ውሳኔ እንዲጸኑ የማድረግ አቅም ምጣኔ | በመቶኛ | 87.3% | 91.5 | 92 | 92.5 | 93 | 93.5 | 94 | 95 | |
| | 99% የደረሰ ዐቃቤ ህግ ይግባኝ የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳይ ውጤታማነት ምጣኔ | በመቶኛ | 89.3% | 93 | 94 | 95 | 96 | 97 | 98 | 99 | |
| | 95% የፀና ተከሳሽ ሰበር የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳይ መዝገቦች ምጣኔ | በመቶኛ | 90% | 91.5 | 92 | 92.5 | 93 | 93.5 | 94 | 95 | |
| | 99% የደረሰ ዓቃቤ ህግ ሰበር የጠየቁባቸው የፍትሐብሔር ጉዳይ መዝገቦች ውጤታማነት ምጣኔ | በመቶኛ | 90% | 93 | 94 | 95 | 96 | 97 | 98 | 99 | |
| **የሰብአዊ መብት አያያዝና ጥበቃ ውጤታማነት ማሳደግ፣** | የሰብዓዊ መብት ድርጊት መርሃ-ግብር አፈፃፀም ሪፖርት ያቀረቡ ፈጻሚ ተቋማት በቁጥር | በቁጥር | 27 | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | 30 | **ፍትህ ቢሮና ማ/ኮሚ ሽን** |
| | ከፈጻሚ ተቋማት በሚቀርቡ ዕቅድና አፈጻጸም ላይ የተደረገ ድጋፍና ክትትል በቁጥር | በዙር | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | |
| | በሰብዓዊ መብት ድርጊት-መርሃ ግብር መነሻነት የተደረገ የአፈጻጸም ግምገማ መድረክ በዙር | በዙር | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |
| | በሰብዓዊ መብት አጠባበቅ ዙሪያ ለፈጻሚዎች የተሰጠ የግንዛቤ ማስጨበጫ በዙር | በዙር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | በሰብዓዊ መብት ህግጋት ዙሪያ ለህብረተሰቡ የተፈጠረ ግንዛቤ በዙር | በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |
| | በማረፊያ ቤት በሚገኙ ተጠርጣሪዎች የተደረገ ጉብኝት በሳምንት | በሳምንት | 98 ጊዜ | 104 ጊዜ | 104 ጊዜ | 104 ጊዜ | 104 ጊዜ | 104 ጊዜ | 104 ጊዜ | 104 ጊዜ | |
| | በማረሚያ ተቋማት በሚገኙ ታራሚዎች የተደረገ ጉብኝት በወራት | በወር | 10 ጊዜ | 12 ጊዜ | 12 ጊዜ | 12 ጊዜ | 12 ጊዜ | 12 ጊዜ | 12 ጊዜ | 12 ጊዜ | |
| | በሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጠያቂ የተደረጉ ሰዎች | በመቶኛ | --- | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| **የህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር መከላከልና ቁጥጥር ውጤታማነትን ማሳደግ** | በሰው መነገድና ሰውን በወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር መከላከል ግብረ-ኃይል የዕቅድና ሪፖርት ግምገማ በዙር | በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | **ፍትህ ቢሮ** |
| | ለታችኛው መዋቅር ግብረ-ኃይል የተደረገ ክትትልና ድጋፍ በዙር | በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |
| | በሰው መነገድና ሰውን በወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር መከላከል ዙሪያ የተዘጋጁ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች በዙር | በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |

| ግብ | የግብ አመልካች/መለኪያ | መስፈሪያ | መነሻ የ2015 በት ዓመት አፈጻጸም | በዕቅድ ዘመኑ የሚደረስባቸው ዒላማዎች | | | | | | | ፈጻሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| | በሰው መነገድና ሰውን በወጥ መንገድ ድንበር ማሻገር ወንጀል ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የተደረጉ ጥናቶች በቁጥር | በዙር | -- | | 1 | | 1 | | 1 | | |
| የህግ ማርቀቅና ምክር አገልግሎት ውጤታማነት ማሳደግ፣ | ተረቀው አስተያየት የተሰጠባቸው ህጎች ምጣኔ | በቁጥር | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | ፍትህ ቢሮ |
| | ወደ እንግሊዘኛ የተተረጎሙ ህጎች ምጣኔ | በቁጥር | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | የተደረገ የህጎች ፋይዳ ጥናት በቁጥር | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | ለመንግስት ተቋማት የተሰጠ የህግ ምክር አገልግሎት በመቶኛ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| የንቃተ ህግ ግንዛቤ አሰጣጥ ውጤታማነትን ማሳደግ፣ | የተደረገ የንቃተ ህግ ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት በቁጥር | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | ፍትህ ቢሮ |
| | የተዘጋጀ 350 የንቃተ ህግ መፍጠሪያ ማንዋል | በቁጥር | 38 | 40 | 43 | 47 | 50 | 53 | 57 | 60 | |
| | በሬድዮ/በኤሌክትሮኒክስ/ ሚዲያ የተላለፈ የንቃተ ሕግ ትምህርት ፕሮግራም ብዛት | በሳምንት | 48 | 52 | 52 | 52 | 52 | 52 | 52 | 52 | |
| | በሬድዮና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ የተላለፈ የንቃተ ሕግ ትምህርት ማስተማሪያ የህግ ርዕስ ብዛት | በቁጥር | 48 | 52 | 52 | 52 | 52 | 52 | 52 | 52 | |
| | በፊት ለፊት መድረክ የንቃተ ህግ ትምህርት የተሰጣቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች በቁጥር | በቁጥር | 415,572 | 440,000 | 460,000 | 480,000 | 500,000 | 520,000 | 540,000 | 560,000 | |
| | በኤሌክትሮኒክ እና በሕትመት ሚዲያ የንቃተ ህግ ትምህርት ያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በቁጥር | በቁጥር (በሚሊዮን) | 2,454,312 | 2.5 | 2.6 | 2.7 | 2.8 | 2.9 | 3 | 3 | |
| | ለታራሚዎች የተሰጠ የንቃተ ሕግ ትምህርት የወሰዱ ታራሚ በቁጥር | በቁጥር | 2,758 | 3,195 | 3,674 | 4,225 | 4,860 | 5,588 | 6,426 | 7,390 | ፍ/ቢ እና ማ/ ኮሚ. |
| | ከክልሉ ዩኒቨርሲቲዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት የተሰጡ ስልጠናዎች፣ | በቁጥር | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | ፍትህ ቢሮ |
| | ተዘጋጅቶ የታተመ የንቃተ ሕግ ማስተማሪያ ቡክሌትና ብሮሸር ብዛት | በኮፒ | --- | 3,500 | 4,000 | 4,000 | 4,500 | 4,500 | 5,000 | 5,000 | |
| | የተሰጡ የንቃተ ህግ ትምህርቶች ባስገኙት ፋይዳ ላይ የተደረገ ጥናት በቁጥር | በቁጥር | -- | **1** | **1** | **1** | **1** | **1** | **1** | **1** | |
| የህጎችን ተደራሽነት ማሳደግ፣ | የተሰበሰቡ ህግጋት በዓ/ም | በዓ/ም | -- | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | ፍትህ ቢሮ |
| | ተጠቃለው የተጠረዙ ህግጋት በኮፒ | በኮፒ | -- | --- | --- | --- | 1,000 | --- | --- | 1,000 | |
| | ተጠቃለዉ ተደራሽ የተደረጉ ህጎች በመቶኛ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| የሰነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎትን ውጤታማነት ማሳደግ፣ | ተረጋግጠው የተመዘገቡ ሰነዶች ብዛት | በቁጥር | 33,257 | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | ፍትህ ቢሮ |
| | የሠነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር የሚዘጋ የአሰራር ስርዓት 100% ማጠናከር፤ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | የሠነዶች ማረጋገጥና ምዝገባ አገልግሎትን በህጉ መሰረት መከናወኑ በየሩብ ዓመቱ ኦዲት ማድረግ፤ | በዙር | | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | |
| | በሰነድ ማረጋገጥና ምዝገባ ዙሪያ የተሰጠ ስልጠና በዙር | በዙር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| የጠበቆችና የግል የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ለፍትህ ሥርዓት አጋዥነታቸው ማጠናከር | የተሰጠ የጥብቅና ፍቃድ ብዛት | በቁጥር | 40 ጠበቆች | ጥያቄ እንደ | ጥያቄ እንደ | ጥያቄ እንደ | ጥያቄ እንደ | ጥያቄ እንደ | ጥያቄ እንደ | ጥያቄ እንደ | ፍትህ ቢሮ |
| | የታደሰ የጥብቅና ፍቃድ በመቶኛ | በመቶኛ | 271 ጠበቆጭ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | በጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ላይ በሚቀርቡ አቤቱታዎች የተሰጠ ውሳኔ ምጣኔ | በመቶኛ | 87.3% | 93% | 94% | 95% | 96% | 97% | 99% | 100% | |

| ግብ | የግብ አመልካች/መለኪያ | መስፈሪያ | መነሻ የ2015 በት ዓመት አፈጻጸም | በዕቅድ ዘመኑ የሚደረስባቸው ዒላማዎች | | | | | | | ፈጻሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| | በጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ላይ በሚቀርቡ ክሶች በዲስፕሊን ጉባኤ የተሰጠ ውሳኔ ምጣኔ | በመቶኛ | 47.4% | 90% | 91% | 92% | 93 | 94 | 95% | 96% | |
| | በስነ-ምግባር ጥሰት ጥፋተኛ ተብለው የተቀጡ ጠበቆችና የግል የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች ምጣኔ | በመቶኛ | 86.2% | 89% | 90% | 91% | 92% | 93% | 94% | 95% | |
| | በስነ-ምግባር እና በሌሎች ርዕሶች ላይ የተሰጡ ስልጠና በዙር | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | ለጠበቆችና ለህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች የተደረገ ክትትልና ድጋፍ በዙር | በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |
| | ለጠበቆችና የህግ ጉዳይ ጸሐፊዎች የተዘጋጁ የውይይት መድረኮች በዙር | በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |
| | ነፃ የጥብቅና አገልግሎት ያገኙ አቅም የሌላቸው ዜጎች በቁጥር | በቁጥር | 3,042 | እንደቀረበ | እንደቀረበ | እንደቀረበ | እንደቀረበ | እንደቀረበ | እንደቀረበ | እንደቀረበ | |
| | 100% ውጤታማ የሆነ ነፃ የጥብቅና አገልግሎት፣ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | የተዘጋጀ ክልላዊ የጠበቆች አስተዳደር አዋጅ | | | | 1 | | | | | | |
| የዜጎችን በሲቪል ማህበራት የመደራጀት መብታቸውን ማረጋገጥ | የተዘጋጀ ክልላዊ የሲቪል ማህበራት አዋጅ | በቁጥር | - | - | 1 | - | - | - | - | - | ፍትህ ቢሮ |
| | የተሰጠ የሲቪክ ማሕበራት ፍቃድ በቁጥር | በቁጥር | 35 ማህበራት | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | እንደ ቀረበ | |
| | የታደሰ የሲቪክ ማሕበራት ፍቃድ በመቶኛ | በመቶኛ | 52 ማህበራት | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | በማህበራት ላይ በሚቀርቡ አቤቱታዎች 100% ምላሽ ምጣኔ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | በሲቪክ ማህበራት ላይ የተደረገ ድጋፍና ክትትል በዙር | በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |
| ለታራሚዎች ተሀድሶ ልማት ግንባታ መስጠት | የቀለም ትምህርት የተማሩ ታራሚዎች በቁጥር | በቁጥር | 2,182 | 2,200 | 2,350 | 2,433 | 2,798 | 3,218 | 3,700 | 4,255 | ማረሚያ ኮሚሽን |
| | በቴክኒክና ሙያ ሥልጠና የሰለጠኑ ታራሚዎ በቁጥር | በቁጥር | 1,327 | 2,000 | 2,149 | 2,224 | 2,891 | 3,758 | 4,880 | 6,352 | |
| | የተገነባ ዘመናዊ የግብርና እና የዕደ ጥበብ ማዕከላት በቁጥር | በቁጥር | | | | | | | 1 | | |
| | የሥነ ዜጋና ሥነ-ምግባር ትምህርት የሰለጠኑ ታራሚዎች በቁጥር | በቁጥር | 3,207 | 3,642 | 4,189 | 4,817 | 5,540 | 6,371 | 7,327 | 8,426 | |
| | የምክክር አገልግሎት ያገኙ ታራሚዎች በቁጥር | በቁጥር | 2,960 | 3,500 | 4,598 | 5,313 | 6,575 | 7,792 | 8,985 | 9,221 | |
| | የኮ-ካውንስለር ስልጠና ያገኙ ታራሚዎች በቁጥር | በቁጥር | 79 | 90 | 100 | 110 | 120 | 130 | 140 | 150 | |
| | ታራሚዎች በየሙያ ዘርፍ በማህበር በማደራጀት የገቢ መጠናቸው 100% ማማደግ፣ | | በመቶኛ | | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | የተቋቋመ የወጣት ጥፋተኞች የተሀድሶ ማዕከል በቁጥር | በቁጥር | | | | | | 1 | | | |
| የታራሚዎች መሰረታዊ ፍላጐት ማሟላት | በሚኒማ መሠረት የቀረበ የምግብ አቅርቦት በመቶኛ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | ማረሚያ ኮሚሽን |
| | የተሟላ የመጠጥና የንጽህና መጠበቂያ ውሃ አቅርቦት በመቶኛ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | የጤና አገልግሎት ያገኙ የህግ ታራሚዎች በመቶኛ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | የተሟላ የህግ ታራሚዎች የመዝናኛ ክበባት በመቶኛ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | የተቋቋመ የሥነ-አእምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል በቁጥር | በቁጥር | | | | | | 1 | | | |
| የታራሚዎች | የተጠናከረ የጥበቃና የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት በመቶኛ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | ማረሚ |

| ግብ | የግብ አመልካች/መለኪያ | መስፈሪያ | መነሻ የ2015 በት ዓመት አፈጻጸም | በዕቅድ ዘመኑ የሚደረስባቸው ዒላማዎች | | | | | | | ፈጻሚ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | 2016 | 2017 | 2018 | 2019 | 2020 | 2021 | 2022 | |
| ደህንነት ማረጋገጥ | ዓላማ፣ ደንብና መመሪያ ያወቁ ታራሚዎች በመቶኛ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | ያ ኮሚሽን |
| | የተያዙ የተከለከሉ ቁሳቁሶች በመቶኛ | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | የተሃድሶ ስልጠና የወሰዱ አባሎች በቁጥር | በቁጥር | 43 | | | 100 | | 100 | | 80 | |
| | አዲስ የሰለጠኑ የማረሚያ ምልምል ፖሊሶች | በቁጥር | 133 | | 150 | | 150 | | 200 | 200 | |
| የፍትህ አካላት የህግ ባለሙያዎች አቅም ማሳደግ | የቅድመ ሥራ ስልጠና የሰለጠኑ የህግ ባለሙያዎች | በቁጥር | 60 | 48 | 48 | 48 | 48 | 48 | 48 | 48 | ፍ/አ/ሥ/ጥ/ማዕ ከል |
| | የሥራ ላይ ስልጠና የሰለጠኑ የህግ ባለሙያዎች | በቁጥር | 64 | 52 | 52 | 52 | 52 | 52 | 52 | 52 | |
| | አጫጭር ስልጣና የሰለጠኑ የህግ ባለሙያዎች | በቁጥር | 350 | 400 | 400 | 400 | 400 | 400 | 400 | 400 | |
| | የተደረገ የስልጠና የፍላጎት ዳሰሳ ጥናት | በቁጠር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | የስልጠና ፋይዳ ማካሄድ | በቁጠር | | | | 1 | | | 1 | | |
| በህጎች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ ውጤታማነታቸው ማረጋገጥ | የምርምር ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | ፍ/አ/ሥ/ጥ/ማ እና ፍትህ ቢሮ |
| | በተመረጡ ህጎች ላይ የተደረገ ጥናት | በቁጥር | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | |
| | በህግ ጥናት ላይ የተሳተፉ ዩኒቨርሲቲዎች፣ | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | የፋይዳ ዳሰሳ የተደረገባቸው የጥናትና ምርምር ውጤቶች | በዙር | | | | | 1 | | | 1 | |
| የፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም ተፈጻሚነት ማረጋገጥ | በፍትህ ማሻሻያ ፕሮግራም ዙሪያ የተሰጠ የማማከር አገልግሎት | በመቶኛ | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | ፍ/አ/ሥ/ጥ/ማ እና ፍትህ ቢሮ |
| | የተዘጋጀ ክልል አቀፍ የፍትህ ሳምንት | በዙር | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 | |
| | በፍትህ ዘርፉ የሚከናወኑ የማሻሻያ ፕሮግራሞች አፈጻጸም ዙሪያ የተደረገ ክትትልና ድጋፍ | በዙር | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | |
| | የተደረገ የፍትህ ተቋማት ጥምረት መድረክ | በዙር | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | |
| | የተሰበሰበ፣ የተተነተነና የተደራጀ የፍትህ መረጃ | በመቶኛ | | 80% | 90% | 100% | 100% | 100% | 100% | 100% | |
| | የፍትህ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ 10ሩ ፒላሮችን መተግበር፤ | በቁጥር | | 1 | 7 | 2 | | | | | 3ቱ ተቋማት |

# ክፍል አራት

## 4. የ7 ዓመት መሪ የልማት ዕቅድ የአፈጻጸም ክትትልና ግምገማ ስርዓት

### 4.1. የክትትልና ግምገማው ዓላማ፡-

- የታቀዱ ስራዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ስለመከናወናቸውና ውጤት ስለማስመስገባቸው ማረጋገጥ፤
- በየደረጃው በዕቅድ አፈጻጸም ሂደት የሚያጋጥሙ ተግዳሮቶችንና የሚስተዋሉ ድክመቶች በወቅቱ በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫ ለማስቀመጥ፤
- በዕቅድ ዘመኑ ተቋሙ ያቀዳቸውን ዕቅዶች ለማሳካት በመንግስት የተበጀተውን በጀት ለታለመለት ዓላማ በማዋል የተቋሙን ተግባርና ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ ለማስቻል፣

### 4.2. የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ ስርዓት

**ክትትልና ድጋፍ፡-** በተቋሙ በ7 ዓመት የልማት ዕቅድ ዘመኑ ለማከናወን የታቀዱ ግቦችን በዕቅዱ መሰረት እየተከናወኑ መሆኑንና እንዲሁም ክንውኑ ተፈላጊውን ውጤት ማስገኘት መቻሉን ለመከታተልና በትግበራ ወቅት የሚያጋጥሙትን ችግሮች በወቅቱ ለመፍታትና ማስተካከያ ለማድረግ በሚያስችለው መልኩ በዓመት፣ በግማሽ ዓመት፣ በየሩብ ዓመቱ እና እንደ አስፈላጊነቱ በየወሩ በአካል በመገኘት ወይም በስልክ ወይም በሚቀርቡ የጽሁፍ ሪፖርት መነሻነት በቡድን ወይም በግለሰብ ደረጃ የሚከናወን ይሆናል፡፡

**ግምገማ፡-** በሴክተሩ በየአስተዳደር እርከን ያሉ ገምጋሚ አካላት የስትራቴጂው አፈጻጸም በታቀደው መሰረት እየተከናወነ መሆኑን በተሟላ መልኩ ለመገምገም እንዲያስችለው በየወቅቱ በሚቀርቡ  የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች፣ የክትትልና ድጋፍ ሪፖርት፣ የተቋምና የሰራተኛ የአፈጻጸም ምዘና ውጤት፣ የዳሳሳ ጥናት፣ የተገልጋዮች ግብረ መልስና የአፈጻጸም መረጃ መነሻት የተለያዩ የግምገማ መደረኮችን በማዘጋጀት አፈጻጸሙን በመገምገምና በታዩ ጥንካሬዎችና ውስንነቶች ላይ ግብረ-መልስ መስጠትን በስልትነት በመጠቀም የሚፈጽሙት ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በድጋፋዊ ክትትል ሂደቱ የተለዩትን ውስንነቶችን ለመቅረፍ ለአመራሩና ፈጻሚው የአጭርና የረጅም ጊዜ የአቅም ግንባታ ስራዎችን በመስራት የሚታዩ ውስንነቶች እንዲቀረፉ ይደረጋል፡፡

በመሆኑም የተቋሙ ስትራቴጂክ ዕቅድ አፈጻጸም የሚከተሉት ዋና ዋና የክትትልና ግምገማ ደረጃዎች አሉት፡፡

## የዕቅድ አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ሥርዓት ማሳያ ሠንጠረዥ

| የክትትልና ግምገማ ፈጻሚዎች | የሚከናወኑ ተግባራት | የክትትልና ግምገማ የሚከናወንበት ጊዜ | ተሳታፊ አካላት |
|---|---|---|---|
| የፍትህ ሴክተሩ አመራር | • በአጠቃላይ ዕቅድን ከአፈፃፀም ጋር እያነፃፀረ እንዲሁም የዓመታዊ ዕቅድ አፈፃፀም ከሚጠበቀው ስትራቴጂያዊ ውጤት አንፃር ይገመገማል፡፡ | • በሴክተር ጉባኤ<br>• በየወቅቱ በሚደረግ አጠቃላይ ውይይት | • የፍትህ ሴክተሩ አመራር፣ ፈጻሚ፣ ባለድርሻ አካላትና የህዝብ ክንፍ |
| የተቋም ማናጅመንት | • የእያንዳንዱ አደረጃጀት ወጥ የሆነ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት የዕቅድ አፈፃፀም መከታተል መገምገም መመዘን፤<br>• ወቅታዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ ስትራቴጂያዊ አካል በማድረግ መተግበር፤ | • በየዕለቱ በሚደረግ የሥራ ግንኙነት፣<br>• በየሩብ ዓመት፣ በስድስት፣ በዘጠኝ ወርና በዓመትቱ መጨረሻ በሚቀርቡ የአፈፃፀም ሪፖርት፤<br>• በተለያየ ወቅት ለሥራ በሚቋቋም ኮሚቴ እና ከባለሙያ በሚቀርብ የመስክ ሪፖርት<br>• ከተገልጋዮች ግብረ- መልስ በተሰጠ ወቅት | • በየአስተዳደር እርከኑ የሚገኙ የማናጅመንት አባላት |
| የተቋም ዳይሬክቶሬቶች እና የዞን፣ የልዩ ወረዳ፣ ወረዳ እና ከተማ አስተዳደር ዐቃቤ ህግ መምሪያ/ጽ/ቤቶች | • የየዕለት ተግባራት ከሚጠበቀው ውጤት አንፃር መገምገም፤<br>• የዕቅድ አፈፃፀም ከዓላማውና ከግብ አንፃር ማየት፤<br>• አጠቃላይ የዕቅደ አፈፃፀም ከሚጠበቀው ስትራቴጂያዊ ውጤት አንፃር ይገመግማል፤<br>• የተቀመጠውን ግብ ያስገኘውን ፋይዳ ይገመግማል፤ | • በሳምንታዊ፣ በ15 ቀን እና በየወሩ በሚደረግ አጠቃላይ ውይይት፤<br>• በሶስት፣ በስድስት. በዘጠኝ ወር እና በየዓመቱ መጨረሻ በሚቀርብ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት፤ | • ዳይሬክቶሬቶች ዳይሬክተር<br>• የስራ ሂደት አስተባሪዎች<br>• የስራ ክፍሉ ሰራተኞች |